# የማንም ጉባዔ

መንግሥቱ ለማ



QQD 892.816
MAN
361,122



# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | ፫ |
| መቅድም | ፭ |
| - ሕይወት | ፲፩ |
| ያፍ ፡ ዘመድ | ፲፬ |
| ትዝታ | ፲፭ |
| - አገሩ ፡ ገቢ | ፲፯ |
| - ውኃ ,ማያጠፋው | ፳፪ |
| - እንዲያው ፡ ዝም | ፳፫ |
| ዓለሙ ፡ ሰልችቶኝ | ፳፬ |
| የፍቅር ፡ ፍላፃ | ፳፭ |
| - ጉድባይ | ፳፯ |
| - ሦስት ፡ ቀን ፡ ሲቀራት | ፳፰ |
| ያገር ፡ ልጅ | ፴፫ |
| መኖር ፡ መላ ፡ አገኘ | ፴፬ |
| ኪስ | ፴፭ |
| - በጠራ ፡ ጨረቃ | ፴፯ |
| - የወንድ ፡ ልጅ ፡ ያለህ | ፴፱ |
| - በገላጋይ | ፵፩ |
| እናትና ፡ ልጅ | ፵፭ |
| ሞኝት ፡ ተላሊት | ፶፩ |
| - ጠላና ፡ ሙዚቃ | ፶፬ |
| ተጣልተን ፡ ተኳርፈን | ፶፭ |
| - ሞትና ፡ መለየት | ፶፯ |
| - ሕንደኬ | ፶፱ |
| ማናሊ | ፷፩ |
| ቦምቤይ | ፷፪ |
| ጉድባይ ፡ ዳግማዊ | ፷፫ |
| ጉባኤ ፡ ቃና | ፷፭ |
| ማስታወሻ | ፷፯ |

# መግቢያ

የግጥም ፡ ጉባኤን ፡ ዳግመኛ ፡ በደምብ ፡ ለማሳተም ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የሆነኝ ፡ በአንባቢዎች ፡ ዘንድ ፡ ያገኘ ችው፡ መልካም፡ አቀባበል ፡ የፈጠረው ፡ ፕሮብሌም፡ ነው። ቢሆንም ፡«የግጥም፡ ጉባኤ»፡ በማይክሎስታይል ፡ ከተራባ ችና ፡ ደራሲዋም ፡ ዲፕሎማት ፡ ከሆነ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ አልፎ ፡ አምስተኛው ፡ መገባደዱም ፡ ተጨማሪ ፡ ምክን ያት ፡ መሆኑ ፡ አልቀረምና ፤ « ዴልሂ— ዋላ » መሆን ፡ መንፈስ ፡ ድርሰትን ፡ የማይገድለው ፡ መሆኑን ፡ ለማብራ ራት ፡ ያህል ፤ ወደ ፡ ብሔረ ፡ ሕንደኬ ፡ ልመጣ ፡ ስልና ፡ ከመጣሁም ፡ በኋላ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሲያሰኘኝ ፡ ከገጠም ኳቸው ፡ «ሕንደኬ» ፡ በሚል ፡ ምዕራፍ ፡ አርእስት ፡ ከቀ ደምቶቹ ፡ ለይቼ ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ላንባቢዎች ፡ አቅርቤአለሁ ። በተረፈ ፡ አንዳንድ ፡ ግድፈት ፡ ከማረምና፡ ከማስተካከል ፡ በቀር ፡ የተለወጠ ፡ የለም ። በመጽሐፉቱ፡ መጨረሻ፡ ማስታወሻ፡ የተደረገላቸውን ፡ ግጥሞች ፡ ከማን በብ ፡ በፊት ፡ በየግጥሙ ፡ አርእስት ፡ ማስታወሻውን ፡ ፈልጎ ፡ መመልከት ፡ አይከፋም ።

በ፲፱፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጻፍኩት ፡ መቅድም ፡ ድርሰታቸ ውን ፡ ማሳተሚያ፡ ገንዘብ ፡ ከማጣት፡ የተነሣ ፡ ደራሲዎች፡ በችግር ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ የመሆናቸውን ፡ ነገር ፡ አንሥቼ፡ ነበር ። በሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ በመጻሕፍት ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ደራሲ ፤ አሳታሚ ፤ አታሚ ፡ አለ ። ከነዚህ ፡ ባለ ፡ ገን ዘብ ፡ መሆን ፡ የሚገባቸው፡ አሳታሚና፡ አታሚ ፡ ናቸው። ደራሲ ፤ ስጦታና ፡ ችሎታ ፡ ካለው ፡ ገንዘብ ፡ ባይኖረው ፡ ግድ ፡ የለም ። ጽሑፉን ፡ ላሳታሚ ፡ (ፐብሊሸር) ፡ ያስረክ

ባል ። አሳታሚ ፣ አሳትሞ ፣ ለሕዝብ ፣ እንዲዳረስ ፣ ያደር ጋል። በሀገራችን ፣ ግን ፣ ደራሲም ፣ አሳታሚም ፣ አንድ ፣ ሰው ፣ መሆን ፣ አለበት። ይህ፣ የተጣመመ፣ ሁኔታ ፣ ሊቃና፣ የሚችለው ፣ አቶ ፣ ወርቁ ፣ ብሩ ፣ በፍቅረ ፣ ንዋይ ፣ ኩታ ቸው፣ ላይ ፣ የፍቅረ ፣ መጻሕፍትን፣ ካባ ፣ ደረብ፣ አድርገው፣ ያሳታሚነቱን ፣ ሸክም ፣ ከኰሳሳው ፣ ደራሲ ፣ ትከሻ ፣ ቢያነ ሱለት ፣ ሳይሆን ፣ ይቀር ፣ ብላችሁ ?

ደራሲው
ኒው ዴልሂ
፲፱፻፶፭ ዓ ም



# መቅድም

ይህችን ፣ ትንሽ ፣ መጽሐፍ ፣ ሳሳትም፤ አንባቢዎቼ፣ በተለይ ፣ የዘመናችን፣ ወጣቶች ፣ መሆናቸውን ፤ እኒሁም፣ ወጣቶች ፣ የማንኛውንም፣ ድርሰት፣ ቢሆን ፣ ፍሬ ፣ ነገሩን፣ እንጂ ፤ የተጻፈበትን፣ ወረቀት፣ ዓይነትና ፣ የፊደል፣ ቅርጽ፣ ከጉዳይ ፣ የሚቈጥሩት ፣ አለመሆናቸውን ፣ አውቄ ነው ።

ባሁኑ ፣ ባለንበት ፣ ጊዜ ፣ ደራሲዎችን ፣ የተጫና ቸው ፣ ችግር ፣ በዝቷል ። ከዚህ ፣ አንደኛው ፤ የጻፉትን፣ ድርሰት ፣ ማሳተሚያ ፣ ገንዘብ ፣ ማጣታቸው ፣ መሆኑን ፣ ማን ፣ የማያውቅ ፣ አለ ? ያለንበት ፣ ሁኔታ ፣ እያንዳንዱን፣ ደራሲ ፣ ያለውዴታው ፣ ባለጸጋ ፣ እንዲሆን ፣ ያስገድደ ዋል ። እኔም ፣ በበኩሌ ፣ ያ ፣ ብልጽግና ፣ የተባለው ፣ ጽድቅ ፣ ከዛሬ ፣ ነገ ፣ ይመጣና ፣ ከድርሰቶቼ ፣ አንዳንዶ ቹን ፣ እንኳ ፣ አሳትማለሁ ፣ ስል ፣ በተስፋ ፣ እስካሁን ፣ ቈየሁ ። ሳይመጣ ፣ ሲቀር ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ከቡራን ፣ አንባ ቢዎችን ፣ እንደዚህ ፣ ባለ ፣ ቀለምና ፣ ወረቀት ፣ የደፈ ርኳቸው ።

በዚች ፣ ትንሽ ፣ መጽሐፍ ፣ የሰበሰብኳቸው ፣ ግጥ ሞች ፣ ሁሉም ፣ ባንድ ፣ ጊዜ ፣ ወይም ፣ ባንድ ፣ ቦታ ፣ የተ ደረሱ ፣ አይደሉም ። ገሚሶቹ፣ በሀገራችን ፣ እኩሌታዎቹ፣ በእንግሊዝ ፣ አገር ፤ የተጻፉ ፣ ናቸው ። የተጻፉበትም ፣ ከ፹፺፣ እስከ፣ ፺ ፣ ዓ፣ ም ፣ ያለው ፣ ጊዜ ፣ ነው።ላንባቢዎች ፣ የቀረቡበት ፣ ተራ ፣ ግን ፣ የፍቅር ፣ የሐሳብ ፣ የጨዋታ ፤ ወይም ፣ የተረት ፣ የሆኑትን ፣ በየወገናቸው ፣ የሚመድብ ፣ ስለሆነ ፤ መጀመሪያ ፣ የተደረሱበትን፣ ተራ፣ አይከተልም። ለምሳሌ ፣ «እናትና ፣ ልጅ» ፣ ከመጀመሪያዎቹ ፣ውስጥ ፣

አንዱ ፤ «በገላጋይ» ፡ ከመጨረሻዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ነው ።

እኒህ ፡ የግጥም ፡ ድርሰቶች ፡ በተለይ ፡ ለዘመናችን ፡ ወጣቶች ፡ለወንዶቹም ፡ ለሴቶቹም ፤ አስደሳች ፡ ምንባብ ፡ እንዲሆኑልኝ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌአለሁ ። የሀገራችን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ በዕድሜአቸው ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ፡ ግን፡ የፍቅር ፡ ግጥሞቹን ፡ አንብበው ፡ እንደ ፡ «ዓይን ፡ አፋርነት» ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ ሳይሰማቸው ፡ አይቀርም ፡ ብዬ ፡ እገምታለሁ ። ምክንያቱም ፡ እኒህ ፡ አዛውንት ፡ የነሼክስፔርን ፡ የነፑሽኪንን ፡የፍቅር ፡ ግጥሞች ፡ ያላነበቡ ፡ በመሆናቸውና ፤ በሀገራችንም ፡ «ሥጋዊ ፡ ፍቅር » ስለሚባለው ፡ የተጻፈ ፡ ድርሰት ፡ እምብዛም ፡ አይደለምና ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ተስፋ ፡ ከመቁረጥ ፡ የራቅሁ ፡ ነኝ ። አዛውንቱና ፡ ሽበቶዎቹ ፡ ሁሉ ፤ ዕድሜውን ፡ ቸሩ ፡ ፈጣሪ ፡ ይስጣቸውና ፤ እንደገና ፡ ወደ ፡ ልጅነት ፡ የሚመለሱ ፡ ስለሆነ፤ ያንዬ ፡ መጽሐፌን ፡ ከዳር፡ እዳር ፡ ያነቡልኛልና። መቄየት፡ የማያመጣው ፡ የለም ። የሐሳብ ፤ የጨዋታ ፤ የተረት ፡ ግጥሞቼ ፡ ግን ፡ ላዋቂውም ፡ ለልጅ ፡ እግሩም ፡ የሚስማሙ ፡ ናቸው ፡ ባይ ፡ ነኝ ።

ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ለተከበራችሁ ፡ አንባቢዎች ፡ የምነግረው ፡ የለኝም።አንብባችሁ ፡ እዩት ። ለያንዳንዱ ፡ ግጥም ፡ የምትሰጡት ፡ ፍችና ፡ ትርጓሜ ፡ ከራሴ ፡ አስተያየት ፡ የተለየ፡ ቢሆንም ፤ ከእናንተ፡ ጠብ ፡ የለኝም ። ብቻ ፡ ላሳስባችሁ ፡ የምፈቅዳት ፡ —ክቡር ፡ ፈቃዳችሁ ፡ ይሁንልኝና— አንዲት ፡ ነገር ፡ አለችኝ ። ይኸውም ፡ አንዱ ፡ መጥፎ ፡ «ደራሲው ፡ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፍ ፡ የጻፈው ፡ የግል፡



ታሪኩን ፡ ነው » ቢላችሁ ፡ በሱ ፡ አሳብ ፡ ከመስማማታችሁ ፡ አስቀድሞ ፡ ሼክስፔርንና ፡ ቤርናርድ—ሾን ፡ እንድ ታስታውሷቸው ፡ ነው ። ሼክስፔርም ፡ ቤርናርድ—ሾም ፡ የቄሣርና ፡ የክሌዎፓትርን ፡ ታሪክ ፡ ድራማ ፡ ጽፈዋል።ሾ ፡ ከሞተ ፡ አንድ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ቢሆነው ፡ ነው ። በሼክስፔር ፡ ዘመንና ፡ በክሌዎፓትራ ፡ ዘመን ፡ መሀከል ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ሺህ ፡ ዓመት ፡ አልፏል ። ሁለቱም ፡ ያላዩትን ፡ ያልነበሩበትን ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ በድራማ ፡ መልክ ፡ የጻፉት ። ይህም ፡ ሆኖ ፤ ዓለም ፡ ለጽሕፈታቸው ፡ አድንቆቱንና ፡ አክብሮቱን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዳበረከተ ፡ አለ ።

## ስለ ፡ ጽሑፉ ፡ አቀራረብ

በየትም ፡ አገር ፡ ቢሆን ፡ ለግጥምና ፡ ለቅኔ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አንዳንድ ፡ ልዩ ፡ መብትና ፡ ነፃነት፡ ተሰጥቷቸዋል። አንዳንድዬ ፡ የሰዋስውን ፡ ሕግ ፡ ቢሰብሩ ፤ አንዳንድዬ ፡ የጽሕፈትን ፡ ደምብ ፡ ባይከተሉ ፤ አንዳንድዬም ፡ ደግሞ ፡ በቋንቋው ፡ የሌለ ፡ ቃል ፡ ፈጥረው ፡ በግጥማቸው ፡ ቢያስገቡ ፤ ያለውንም ፡ ቢለውጡት ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ «የባለ ፡ ቅኔዎች ፡ ነፃነት» ፡ ተብሎ ፡ ታውቆላቸዋል ። ይህ ፡ መልካም፡ ልማድ ፡ በሀገራችንም ፡ ሳይበዛ ፡ ቢሠራበት ፡ ደግ ፡ ነው።

እኔም ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ « ውሀ ፡ የማያጠፋው » የሚለውን ፡ «ውሀ፡ ,ማያጠፋው» ፡ «እርስ ፡ በርሱ» ፡ የሚለውን ፡ «እስበሱ» ፡ ብዬዋለሁ ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ይገኛል ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ። ይህም ፡ በእንግሊዝኛና ፡

በፈረንሣይኛ ፡ ግጥም ፡ የተለመደ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ አዲስ ፡ አሳብ ፡ አይደለም ። አንዱን ፡ ቃል ፡ ሙሉውን ፡ መጻፉ ፤ የግጥም ፡ ዜማ፡ የሚሰብር ፡ ሲሆን፤ አንድ፡ ሁለት ፡ ቀለም፡ ቢገድፉለትና ፡ የተደገፈበትን ፡ ቦታ ፡ ባንድ ፡ ዓይነት ፡ ምልክት ፡ ቢያሳዩ ፡ አያስነቅፍም ፡ በግጥም ፤ በቅኔ። እና ንተም ፡ አንባቢዎቼ ፤ «አስተውሎ» ፡ በሰዋስው ፡ ደንብ ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ሊሆን ፡ ሲገባው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፤ «አመል ማሎ» ፡ ደግሞ ፡ «አመልማል» ፡ ተብሎ ፡ ብታገኙ ፤ ምክ ንያቱ ፡ የባለ ፡ ቅኔ ፡ ነፃነት ፡ መሆኑን ፡ ታውቁታላችሁ ።

ደራሲው
አዲስ አበባ
፲፱፻፶ ዓ ም



ፍቅርን ፡ በምንም ፡ ለምንም
ለማይለውጡ
ሁሉ

. . . . . . . . መቼስ ፡ ባለቅኔን ፡ ይፈታተኑታል ?
እንዳሻው ፡ ሊናገር ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ።
ሁሉንም ፡ አጣፍጦ ፡ ሊያሰማን ፡ አፍ ፡ አለው ።
ሲያማ ፤ ሰዉ ፡ ቀርቶ ፤ እግዜሩም ፡ አይተርፈው !

«የዝጌር ፡ ጸድቅ»
ከተባለው ልብ ወለድ ድርሰት



## ሕይወት *

ምንድነው ፡ ሰበቡ ፤
ለምንድነው ፡ አላኩኝ ፡ ለምን ፡ ምክንያት ፡
ይህ ፡ ዓለም ፡ መኖሩ —አዱኛ—ሕይወት ፤
ሕፃን ፡ መወለዱ ፡ አርጅቶ ፡ ሊሞት

ለምንድነው ፡ አልኩኝ ፡
ለምን ፡ ምክንያት ።

ማን ፡ ያውቃል ፡ እንዳለው ፡ ለቋጥኝስ ፡ ቋንቋ ?
ዛፍ ፡ ለሚቈረጥ ፡ ዛፍ ፡ እንዳይቆም ፡ ጠበቃ ፡

ማን ፡ ያውቃል ?

የመስቀል ፡ ወፍና ፡ የአደይ ፡ አበባ ፡
ቀጠሮ ፡ እንዳላቸው ፡ መስከረም ፡ ሲጠባ

ማን ፡ ያውቃል ?

ማን ፡ ይፈትልለታል ፡ ልብሱን ፡ ለድንጋይ ?

ሰው ፡ ሳይዘራ ፡ ሳይተክል ፡ አያመርትምና ፤
ሔዋን ፡ ሳትኖር ፡ አዳም ፡ ልጅ ፡ አይወልድምና ፤

ምክንያቱን ፡ ይሻል ፡ ለሚታየው ፡ ሁሉ ፤
እንዲያው ፤ ለግብር ፡ ይውጣ ፤ ለወጉ ፤ ላመሉ ።

*ይህ ምልክት ለተደረገባቸው የግጥም አርእስቶች በመጽሐፉ መጨረሻ ማስታወሻ ተጽፎላቸዋል ።

ሦቅራጥስ ፡ አፍላጦን ፡ ሙሴና ፡ ዳዊት ፤
ያለም ፡ ፈላስፋዎች ፡ ያለም ፡ ነቢያት ፤
የትናንቶቹና ፡ የትናንቱ ፡ በስቲያ ፡
የዚያ ፡ የዚህ ፡ ወዲያ . . . ወዲያ . . . ወዲያ ፤ ወዲያ !
ልቤ ፡ ተስፋን ፡ ቈርጧል ፡ እናንተን ፡ አይቼ ።
ግና ፡ ሁሉ ፡ ሲሞት ፡ ልብ ፡ ይሞታል ፡ መቼ ?

ስሕተት ፡ ነው ፡ መሰለኝ ፡ ሰበቡን ፡ መሻት ፡
«ለምንድነው» ፡ ማለት ፡ «ለምን ፡ ምክንያት» ።
ለምንድነው ፡ አንበል ?
«ለ»ን ፡ እንግደፋት ?
ታዲያ ፡ ዓለም ፡ ምንድነች ፤ ምንድናት ፡ ሕይወት ?
የሆነችው ፡ በዛ ፤ይህ ፡ ነች ፡ አንላት ፤
—ራሴም ፤ ጥያቄየም፤ የሕይወት ፡ ደቂቃ ፤
የሕይወት ፡ ኬክሮስ ፡ ነን ፤ አለቀ ፡ በቃ ።

ከንቱ ፡ ነው ፡ ወዳጄ ፡ መተርጐም ፡ ማተት ፡
«ይህ ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ሆነ» ፡ «ስለዚህ »ማለት ።
መልሳችን ፡ ዝም ፡ ሊሆን ፤ ላናውቀው ፤ አንልፋ ፤
ከዝም ፡ ለበለጠው ፡ ራሳችን ፡ ይደፋ ፤

ግሩም ፡ ነው ፡ አንበል ፤ ከንቱ ፡ ነው ፡ አንበል ፤
ድንቅ ፡ ነው ፡ አንበል ፡ ዕፁብ ፡ ነው ፡ አንበል ፤
ታምር ፡ ነው ፡ አንበል ፤ አንበል ፡ ነው ፡ ቆንጆ ፤
መፍርሀ ፡ ነው ፡ አንበል ፡ መርዕድ ፡ መደንግፅ ።



ላንቃ ፡ እስኪሰነጠቅ ፡ ምላስ ፡ እስኪነቃ ፡
የሚባለው ፡ ሁሉ ፡ ቢደመር ፡ ላይበቃ ፤
ግሩም ፡ ነው ፡ አንበል ፤
ድንቅ ፡ ነው ፡ አንበል ።
አጥጋቢም ፡ አይደለ ፡ ያውም ፡ ዝም ፡ እንኳን ፤
—ጋን ፡ ሲታጣ ፡ ጊዜ ፡ ምንቸት ፡ ይሁን ፡ ጋን —
እንዲያው ፡ እንደመም ፤
ቃል ፡ ፍሬ ፡ ላይሆን
ካፋችን ፡ አይውጣ ፤ ሕይወት ፡ አትርከስ ፤
አለዚያ ፡ አይቻልም ፡ የሕሊና ፡ ክስ ።

## ያፍ ዘመድ

ዝምም ፡ ያለው ፡ ዘመዴ ፡ እኔ ፡ ሳጣጥር ፡
ሞተ ፡ ቢሉት ፡ መጣ ፡ አልቅሶ ፡ ሊቀብር ።
እኔም ፡ ሙቼ ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ስላየሁ ፡
በመንፈስ ፡ ነድጄ ፡ ተቃጥዬ ፡ ጨስሁ ።
የልቤን ፡ እንዳደርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ
ሆኖ ፤ ተነሥቼ ፡ እነሱ ፡ ሲያረግዱ ፡
እንዲህ ፡ አልኩት ፡ ዘመድ ፡ የተባለውን ፡

«ታምሜ ፡ ነበረ ፡ ሳጣጥር ፡ ማዘን ፤
«አሁን ፡ ክንዴ ፡ ክንዴ ፡ ቀኝ ፡ እጄ ፡ ቢሉኝ ፡
«አሁን ፡ የናቴ ፡ ልጅ ፡ ወንድሜ ፡ ቢሉኝ ፡
«ከሞትኩኝ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ አይገባኝ ።
«ይልቅ ፡ ልተኛበት ፡ አታደንቁረኝ »

ይህን ፡ ተናግሬ ፡ አንጀቴን ፡ አርሼ ፡
ወደ ፡ መጣሁበት ፡ ሄድኩኝ ፡ ተመልሼ ።



## ትዝታ *

ባቡር ፡ ይዞኝ ፡ ሄደ ፡ ከሎንዶን ፡ አውጥቶ ፡
ከጭስ ፡ ከጭጋጉ ፡ ከትቢያው ፡ ለይቶ ፤
ጥላቱን ፡ ደባልቆ ፡ ከከሰል ፡ አቡዋራ ፡
ከእንፋለት ፡ አመልማል ፡ ጉሙን ፡ እያደራ ፡
አገሩን ፡ አልብሶት ፡ ጽድቅና ፡ ኩነኔ ፡
«ይገፎ — ከተፍ» ፡ ይላል ፡ ኃይለኛው ፡ ሸማኔ ።

ግሩም—ድንቅ ፡ —ዕፁብ ፡ ናት ፡ ታምር ፡ ናት ፡ ሕይወት፡
ከከሰል ፡ ጢስ ፡ ማምለጥ ፡ በከሰል ፡ ጉልበት ።

በፉርጎው ፡ ነበረ ፡ ላሥር ፡ ሰው ፡ ወንበር ፤
ሙቀቴ ፡ እንዳይባክን ፡
መለስ ፡ ያረግሁትን ፡ የፉርጎውን ፡ በር ፡
ታጣና ፡ ,ሚከፍተው ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ደፋር ፡
ሥፍራ ፡ እያለ ፡ ጠፍቶ ፡ ሰው ፡ ተደረደረ ፡
ከውጭው ፡ ከብርዱ ፤ መግባት ፡ እያፈረ
ከተዘጋው ፡ ፉርጎ ፡ ጥቁር ፡ ካለበት ።
—ከሰልም ፡ ጥቁር ፡ ነው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕይወት ፡
የብልጽግናዋ ፡ መደብ ፡ መሠረት ።

በዋሽንቱ ፡ አፉጭ ፡ ዘፈነ ፡ ባቡር ፡
ከሩቅ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ፡ የድርቆሽ ፡ ክምር ፡
ነፍሴም ፡ ዘላ ፡ ገባች ፡ ካገሬ ፡ መንደር ፤
ባረንጓዴው ፡ ሜዳ ፡ በእንግሊዝ ፡ ገጠር ፡
በቅጽበት ፡ ሆንኩና ፡ «የዝጌር ፡ መንገደኛ» ፡
«ጤና ፡ ይስጥልኝ ፤ ቤቶች»
—ጥቁር ፡ እንግዳቸው ፡ መጽደቂያቸው ፡ ነኝ!

«ግባ ፣ ቤት ፡ ለእንግዳ ! » አለኝ ፡ ባለቤቱ ፣
ሙቅ ፡ ውሀ ፡ አቀረበች ፡ በቆሬ ፡ ሚስቲቱ ፣
ደስ ፡ ደስ ፡ እያላት ፣ ተምበርካ ፡ እፊቴ ፡
እግሬን ፡ አጠበችው ፡ —«አትግደርደሩ ፡ እቴ ! »

ላንቃዬም ፡ ባረከው ፡ ያን ፡ የጐጃም ፡ ጠላ ፣
ገበታ ፡ ቀረበ ፣ የሆዴ ፡ ቋት ፡ መላ ፣
ጣቴን ፡ ቈረጠምኩት ፡ —የጐንደሬ ፡ ተልባ —
በእርጎ ፡ እየታጀበ ፡ የዶሮው ፡ ወጥ ፡ ገባ ።
ስጠግብ ፡ አዛጋሁ ፡ እንቅልፌ ፡ መጣና ፣
አስተኛኝ ፡ ደርበው ፡ ቡሉኮ ፡ ላይ ፡ ባና ።

በር ፡ ሲከፈት ፡ ሰማሁ ፣ ነቃሁኝ ፡ ሲዘጋ ።
በርዶልኝ ፡ ንዴቱ ፡ መንፈሴ ፡ እንደረጋ ፡
ገላመጥኩት ፡ ባይኔ ፡ ጀግናውን ፡ ወጣት ፡
የገባውን ፡ ደፍሮ ፡ ከተኛሁበት ።
ሸሚዙን ፡ አይቼስ ፡ ከነክራባቱ ፣
ፈገግ ፡ አለው ፡ ፊቴን ፣
አሳቀኝ—ጥዷቱ ።



# አገሩ ገቢ *

የሰማይ ፡ ባቡርም ፡ አጓራ ፡ አኰረፈ ፣
ልብረር ፡ ልብረር ፡ አለና ፡ ተንዘፈዘፈ ።

ጥርሱን ፡ ነከሰና ፡ ሎጋውን ፡ አንገት
ቈልሞ ፣ መለሰው ፡ ዐይኑን ፡ ከመስኮት፡
የመስቀል ፡ ወፍ ፡ ወንድም ፡ ያበሻው ፡ ወጣት ።
እንባ ፡ ዓይኑን ፡ መልቶታል ፡
እንቅርቱን አንቆታል ፣
ያገር ፡ የወንዝ ፡ ልጅ ፡ ደህና ፡ ሁን ፡ ይሉታል
መሐርባቸውን ፡ ያውለበልቡታል ።
ድምፃቸው ፡ ቢሳነው ፡
ቂዛዛውን ፡ ዘልቆ ፡ ከጆሮው ፡ መድረሱ ፣
ይህ ፡ አላወከውም ፣ ባይኑ ፡ ሰማው ፡ እሱ ።

የሰማይ ፡ ባቡርም ፡ ባየር ፡ ተንሣፈፈ ፣
ጉሙን ፡ ቃኘው ፣ዋኘው ፣ነፋስን ቀዘፈ ፣
—ዓይኑ ፡ ደመና ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ አረፈ ።
«...ሎንዶን ፡ ደህና ፡ ሁኚ ....
«...የእንግሊዝ ፡ አገር ... »
እንዳለ ፡ ታወሰው ፡ ያገሩ ፡ ነገር ፣
የሰጡት ፡ አደራ ፡ የዜማው ፡ መዓርግ ፡
የነጮችን ፡ አስማት ፡ ምትሃት ፡ እንዲማር ፡
የዛሬ ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ ካገሩ ፡ ሲወጣ ፡
«ትምህርትን ፡ ሊመገብ»
«ዕውቀትን ፡ ሊጠጣ»

ፈረንጅ ፡ አገር ፡ ሔዶ ፡ ሥልጣኔን ፡ ሊያመጣ ፤
እናቱ ፡ አልቻለችም ፡ ልትሸኘው ፡ ልትመጣ ።

ሳይሆን ፡ ለምንግዴ ፡ ወይም ፡ ለስንፍና ፤
እናት ፤ምንም ፡ ብትሆን ፤ ያው ፡ እናት ፡ ናትና ።
አይሉት ፤ አይደለ ፤ ጥሬ ፡ ድንቁርና ፡
አሻፈረኝ ፡ ብላ ፡
ለጋባዥ ፡ አቅታ ፡
ከቤቷ ፡ መቅረቷ ።

አልታያትም ፡ ሳትሞት ፤ ቁማ ፡ መመልከቷ ፡
ውኃው ፡ ሳይፈጂስ ፡ ያይኗ ፡ ሳይቀልጥም ፡ ብረቷ ፤
ይዞት ፡ የበረረው ፡ የብረት አሞራ ፤
ከምድር ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፤ ሳይጋርደው ፡ ጋራ ፤
ከጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፤ኰረብታ ፡ ተራራ ፡
ባልዞረበት ፡ አገር ፤ ቅልጥ ፡ ባለው ፡ ብራ ፤
በደራ ፡ አደባባይ ፤ ሰው ፡ ሲያየው ፤ በይፋ ፤
ቦግ ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ በቅጽበት ፡ ሲጠፋ ።

አልታያትም ..../

የሆዷን ፡ ሳወቀው ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ፍርሐቷ ፤
ገሚስ ፡ ኑፋቄ ፡ ነው ፡
«አይዞኝ ፤ይመለሳል ፤ ልጄ »ብላ ፡ እምነቷ ።

የብረቱ ፡ አሞራስ ፡ ምድር ፡ ምድር ፡ ሲያይ ፡
ቢጋጭማ ፡ ደርሶ ፡
ከረጋው ፡ ውሃ ፡ ጋር ፤ ከጥቁሩ ፡ ሰማይ!



የሚያበረው ፡ ሴጣን ፡ በክንፉ ፡ ላይ ፡ ታሥሮ ፡
የሚያከንፈው ፡ ጋኔን ፡ ተቈጥቶ ፡ አምሮ
—ነጆቹ ፡ ዘንግተው ፡ ምሱን ፡ ሳይሰጡት—
ምን ፡ ይኗል ፡ ቢያረገው ፡ ለዘንዶቹ ፡ ራት ፤
ለኒያ ፤ተነካክሰው ፡ ጅራት ፡ ለጅራት ፡
ለዚች ፡ ላለማችን ፡ ለሆኗት ፡ ማቶት ፤
እንዳይፈርስ ፡ አፈሯ ፡ የዚች ፡ የመሬት ፡
አጥብቀው ፡ አጥንተው ፡ ለሚጠብቋት ፤
ምን ፡ ይኗል ፡ ቢያረገው ፡ ለዘንዶቹ ፡ ራት ?

«ኢያእምሮሽ ፡ ንጹህ ፤
«እምነትሽ ፡ ነው ፡ ባዕዴ ።
«አንቺ ፡ ግን ፡ —ዘመዴ ... ዘመዴ .. ዘመዴ »

«መማርስ ፤ መሥራት ፡ ነው ፡ መድፉን ፡ ከብረት ፤
«መማርስ ፤መሥራት ፡ ነው ፡ ታንኩን ፡ ከብረት ፤
«መማርስ ፤ መሥራት ፡ ነው ፡ አውሮፕላውን ! »
ብለውት ፡ ነበረ ፡ ሲሰናበቱት ፡
ፊታውራሪ ፡ ባልቻ ፡ መራገፉ ፤ ተኳሹ ፤
ጐበዝ ፤ ያልተባሉ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሸሹ ።
«አፍ ፡ ብቻ» መሆን ፡ ነው ፡ መማር ፡ ቋንቋ ፡ ብቻ !
ብለው ፡ ነበርና ፡ ፊታውራሪ ፡ ባልቻ ።
እሱም ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ «አሜን ፡ ወአሜን ፤
ለይኩን ፡ ለይኩን—ፈቃድህ ይሁን »
የዛሬ ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ ካገሩ ፡ ሲወጣ ፡
«ጥበብን ፡ ለመቅሰም » አንጐሉን ፡ ሲቃጣ ።

እንዲያ ፡ የጣፈጠው ፡ ማርና ፡ ወተት
እንዴህ ፡ በልጦ ፡ ሊገኝ ፡ ምረቱ ፡ ከሬት ።

ሰው ፡ በሚያውቀው ፡ መጠን ፤ እንደልጅነቱ ፤
«ይሆናል» ፡ የሚለው ፡ ይርቃል ፡ ከእውነቱ ።

የሰማይ ፡ ባቡርም ፡ ይንዣበብ ፡ ጀመረ
—ጥምብ ፡ እንዳየ ፡ ጆፌ —
«ይገፍ ፡ ከተፍ» ፡ ባለው ፡ ይመስል ፡ ያፈረ ።

የታል ፡ ታዲያ ፡ ታንኩ ?
መድፉሳ ፡ የት ፡ ቀረ ?
ምን ፡ ሲሠራ ፡ ኑሯል ፡ ዓሥር ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ?
—ቀለህ ፡ እንኳን ፡ ሳይዝ ፡ ነው ፡ የተመለሰ —
በሱ ፡ የጠፋ ፡ ገንዘብ ፡ ከገደል ፡ ፈሰሰ ?

ያንተ ፡ ግን ፤ ያገር ፡ ልጅ ፤
ፍርድህ ፡ ይሰመር ፡ ይቅና ፤
ያምስት ፡ መቶ ፡ ዓመቱን ፡ የሺ ፡ ዓመት ፡ ጐዳና ፡
ተራምዶት ፡ ገደሉን ፡ ተሻግሮታልና ።

ስማኝ ፡ የወንዜ ፡ ልጅ ።
ማወቅም ፡ ጫካ ፡ ነው ፡ ችምችም ፡ ያለው ፡ ዱር ፤
ብርሃን ፤ እንጸብርቆ ፡ ዓይን ፡ የሚሠውር ፤
አዞ ፡ አረግ ፡ ያለበት ፡ እጅ ፡ እግር ፡ የሚያስር ፤
አለ ፡ አሳብ ፡ አንበሳው ፡ አጥንት ፡ የሚሰብር ።

ማወቅም ፡ ጫካ ፡ ነው ፤
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከገቡት ፡ የሌለበት ፡ መውጫ ፡



እንድ ፡ ጊዜ ፡ ከያዘም ፡ የሌለው ፡ ማምለጫ ።
መቶ ፡ ሺህ ፡ መንታ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ጫካ ፡ መንገዱ ፤
ያም ፡ ቢያስኬድ ፤ ያም ፡ ቢያስሄድ ፤ መዳኛው ፡ ነው ፡ አንዱ ።

ልንገርህ ፡ ያገር ፡ ልጅ ፤
ምሥጢሩን ፡ ዕወቀው—
ሞት ፡ አይቀርም ፤ ሞቶ ፡ አምላክ ፡ ቢጠይቀው ፡
ብሎ ፡ «በምድር ፡ ከቶ ፡ ኑረሃል ፡ በውነቱ
እንደውነተኛው ፡ ሰው ፤ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ከብቱ?»
የሱ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ መልሱ ፡—
«አዎን ፤ ጌታ ፡ አዎን»

መድፍ ፡ አልሠራህ ፡ ብለሁ ፡ አትቈጡት ፡ ሊቄ ፤
ጠይቋል ፤ መልሷል ፤ ታላላቅ ፡ ጥያቄ ።
ደሞ ፡ እርስዎም ፤ ሐጂ ፤ አይበሉት ፡ አበድክ
ተላጭቷል ፡ ቢልዎት ፡ ጽሕመ ፡ አሮኑን ፡ ቱርክ ።

# ውኃ, ማያጠፋው *

ውኃ ,ማያጠፋው ፡ እሳት ፡ ነው ፡ ፍቅርሽ ።
ነደድኩኝ ።
ቢል ፡ አልኩኝ ።
ተቃጠልኩልሽ ።
ወደድኩሽ ።
ወደድኩህ ፡ በይኝ ፡ እባክሽ ።



# እንዲያው ዝም

, ወድሻለሁ ፡ ማለት ፡ አይጠቅም፤አይበቃ ፤
ፍቅሬ ፡ ነሽ ፡ ማለትም ፡ አይጠቅም ፤ አይበቃ ፤
ነፍሴ ፡ ነሽ ፡ ማለትም ፡ ልቤን ፡ አያርሰው ፤
የፍቅራችን ፡ ነገር ፡ ዝም ፡ ነው ፤ ዝም ፡ ነው ፤ ።

ምን ፡ ሳርገው ፡ መውደዴን ፡ ለመግለጽ ፡ በሙሉ ?
ልሳምሽ ፡ ፤ ልቀፍሽ ፡ ፤ ላልቅስ ፡ ወይ ፡ ላሙሉ ?
እግርሽን ፡ ልሳም ፡ ወይ ፤ ልስገድልሽ ፡ ወይ ?
ዓዋጅ ፡ ልናገረው ፡ በያደባባይ ?
ወረቀት ፡ ልጻፍ ፡ ወይ ፤ ልላክ ፡ ወይ ፡ ደብዳቤ ፡
እያንዳንዱን ፡ ቃላት ፡ ወልጄ ፡ ከልቤ ፤ ?
ገንዘቤን ፡ ልስጥሽ ፡ ወይ ፡ ሳይቆጨኝ ፡ መክሰሬ ?
ልታረድ ፡ ልሰዋ ፤ ለፍቅርሽ ፡ ለፍቅሬ ?

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው
የልብ ፡ አያደርስም ።
በቃል ፡ ወይ ፡ በሥራ ፡ ፍቅር ፡ አይገለጽም ።
ይሻላል ፡ መሰለኝ ፡ እንዲያው ፡ ዝም ፡ እንዲያው ፡ ዝም፤
እንዲያው ፡ በደፈና ፡ ፤ እንደ ፡ ሃይማኖት ፤
ፍቅሬን ፡ ማወቅሽን ፡ ማመን ፡ መረዳት ።

## ዓለሙ ሰልችቶኝ

ዓለሙ ፡ ሰልችቶኝ፡ ሰዉ ፡ ሴቱ ፡ ወንዱ ፡
ሐበሻው ፡ ፈረንጁ ፡ ትግሬው ፡ አማራው
አዳሜ ፡ ባጭሩ ፤
ነገር ፡ ክርክር
ፌዙ ፡ ቀልዱ ፡ ሣቁ ፡ ፉከራው ፡ ጉራው ፡

ሽሙጥና ፡ አሽሙሩ ፡ ሐሜቱ ፡ ቅናቱ ፡
አለመስማማት ፡
አለመግባባት ፤

ዛፍና ፡ ቅጠሉን ፡ ሰማዩን ፡ ለማየት ፡
የሣሩን ፡ መዓዛ ፡ ሽቶውን ፡ ለማሽተት ፡
እዚያ ፡ ለመንጋለል ፡ ካሳብ ፡ ለማረፍ ፡
በተንቀገርቀገር ፡ ውኃፍ ፡ ልለከፍ
ማረፊያ ፡ ለመሆን ፡ ለርግቦቹ ፡ ኩስ ፡
ለማጨመታተር ፡ የሱሬየን ፡ ተኩስ ፡
የመንፈስ ፡ ጸጥታን ፡ ሰላምን ፡ አደን
ወደ ፡ ሜካው ፡ ገባሁ ፡ ታቅፌሽ ፡ አንቺን ።



## የፍቅር ፍላፃ

ፈረንሣይ ፡ እንግሊዝ ፡ ጀርመን ፡ ጣልያን ፡
ስትጽፍ ፤ ስትናገር ፡ አይዛት ፡ አፏን ፡
ባርኔጣዋ ፡ ሠፊድ ፡ በፓሪሱ ፡ ቁንጥ ፡
የጫማ ፡ ተረከዝ ፡ ስንዝር ፡ የሚበልጥ ፡
ሥልጡን ፤የተማረች ፤ የሠለጠነች ...
ብለው ፡ ሲወድሱሽ ፡ ሲሸሙሽ ፡ ሰዎች ፤

አንዱ ፡ በቢዩክ ፡ መጥቶ ፡ «እንውጣ» ፡ ሲልሽ ፤
በሼቭሮሌት ፡ አንዱ ፡ ሲያንሸረሽርሽ ፤

መዳብ ፡ ያለው ፡ ብሩን ፤ ወርቅ ፡ ያለው ፡ ዕንቁን ፡
የራስ ፡ አክሊል ፡ ያለው ፡ ሲሰጥሽ ፡ ዘውዱን ፤
ማጉገስ ፡ የሚያውቅም ፡ ሲዘፍን ፡ ያንቺን ፡ ስም ፤
,ወድሻለሁ ፡ ያለሽ ፡ ሲሸለም ፡ ሲሾም ፤

በፍቅርሽ ፡ ፍላፃ ፡ ተነድፎ ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡
ሚስቱን ፤ ያገባትን ፡ ምሎ ፡ ተፈጥሞ ፤
ሲያባርር ፡ ሲፈታ ፡ ልጆች ፡ እያሉት ፡
ትዳሩን ፡ ሲያፈርሰው ፡ አንቺን ፡ ለማግባት ፤

እንዳላየ ፡ ዓይቼ ፡
ሰምቼ ፡ እንዳልሰማ ፡
በፈላስፋ ፡ ትዕግሥት ፡ ስቀር ፡ ሳልሻማ ፤
በኋያ ፡ ሁሉ ፡ ልብሽ ፡ ቢጨክን ፡ ቢጠም ፤
ከንፈርሽ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ከንፈር ፡ ባይገጥም ፤
ፍቅርሽ ፡ ተፈትኖ ፡ በገንዘብ ፡ በእሳቱ ፡
ታወቀ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ጥሩ ፡ ወርቅነቱ ።

# ጉድባይ *

ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኚ ።
ጥፋቱስ ፡ አይደለም ፡ ያንቺ ፡ ወይም ፡ ከኔ ፡
ፍቅር ፡ የመሆኑ ፡ ጽድቅና ፡ ኩነኔ ፤
አንቺ ፡ አንቺን ፡ መሆንሽ ፡ እኔ ፡ እኔን ፡ መሆኔ ፤
ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኚ ።

ሰላም ፡ ይሁን ፡ ይላል ፡ ልቤ ፡ ለልብሽ ፤
ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኚ ።

ሳሚልኝ ፡ አደራ ፡ ከንፈሮችሽን ፡
ወለላና ፡ ወተት ፡ የሚያወዙትን ፤
ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኚ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ አይሆንም ፡ ብንገናኝ ፤
ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኚ ።

ስትዞሪው ፡ ዛሬ ፡
የናፍቆቱን ፡ ጋራ ፡ የጠቡን ፡ ተራራ ፡
እንድታደርሽልኝ ፡ መላከቴን ፡ አደራ ፡
ለነሜት ፡ ታዛቢ ፡ ለናቶ ፡ አስተዋይ —
«ጆሮ ፡ ያለው ፡ ይስማኝ ፤ ዓይንም ፡ ያለው ፡ ይይ ፤

ፍቅርም ፡ እንደ ፡ ሰው ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ከብት ፤
እንዳትክልት ፤ እንዳብቁልት ፤ እንደ ፡ ወፍ ፤ እንዳሣ ፡
ደግሞ ፡ እንደ ፡ ነፍሳት ፤
—ችቦ ፡ አብርቶ ፡ በርቶ ፡ እንዲሆን ፡ ጥላት ፡
የመስቀል ፡ ደመራ ፡ ያውዳመቱ ፡ ለት ፡
ዓደይ ፡ ተኰናንባ ፡ ስትስቅ ፡ መሬት —
ፍቅርም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡



ተወልዶ ፤ ነፍስ ፡ አውቆ ፤ ጐርምሶ ፤ ጐልምሶ ፤
ግትቻ ፡ ይሆናል ፡ ደሞ ፡ ተመልሶ ።
ንዝንዝ ፡ ይሆናል ፡
ጭቅጭቅ ፡ ይሆናል ፤
ዓይን ፡ ይደፈርሳል ፤ ማዕበሉም ፡ ያይላል ።

ባሕሪን ፡ መገሠጽ ፡ ነው ፡ ለዚህ ፡ መድኃኒቱ ።
ለሰው ፡ ልጅ ፡ እንጂ ፡ ነው ፡ ፍርቅም ፡ መሠራቱ ፡
እንዲቈነጅና ፡ እንዲያብብ ፡ ሕይወቱ ።

የሰሎሞን ፡ እሳት ፡ ሥጋዊ ፡ ፍቅር ፡
ማሞቁም ፡ ማድመቁም ፡ ማብራቱም ፡ ማብላቱም ፡
ያ ፡ ሁሉ ፡ ሲቀር ፤
ለኩሶ ፡ አያይዞ ፤ አናዶ ፤ ሲያጨስ ፤
ሆድን ፡ ሲያቃጥለው ፤ አንጀት ፡ ሲያሳርር ፤
ትንፋሽን ፡ መርዞ ፡ ላንቃን ፡ ሲያንሜርር ፤
ሴት ፡ ኳኳቴ ፡ ስትሆን ፡ ጭክ ፡ እንዳለች ፡ ዶሮ ፤
አውራው ፡ ማምለጥ ፡ ሲመኝ ፡ ከሚላ ፡ ጋር ፡ በሮ ፤
ያን ፡ ጊዜያት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡
ማሳየት ፡ አለበት ፡ እንዳለው ፡ አእምሮ»

ጉድባይ ፤
ደህና ፡ ሁኚ ።

# ሦስት ቀን ሲቀራት

ወንዙ ፡ ወንዟ ፡ አይደለም ፤
አገሯና ፡ አገሩ ፡
አይነጻጸርም ፡ ቢበሩ ፡ ቢበሩ ።

የወፍ ፡ አፍ ፡ ነው ፡ ቋንቋው ፡
ለፈርጣማው ፡ ጀሮ ፤
ቋንቋዋን ፡ ያወቀው ፡ ለፍቶ ፡ ነው ፡ ተምሮ ።

የሷ ፡ ቤቷ ፡ ቢሆን ፡ የመሬት ፡ እምብርት ፡
የሱ ፡ ቤት ፡ ጀርባ ፡ ነው ፡
—ዓይንና ፡ መሬት ።

የሷ ፡ ጸጉሯ፡ ብጫ ፡
የሱ ፡ በርኖስ ፡ ጠጉር ፤
ዓይኗ ፡ ሰማያዊ ፤ ዓይኑ ፡ ኩል ፡ ጥቁር ።
ጸጉሯ ፡ እንደ ፡ ሐር ፡ ነው ፡
ጐፈሬው ፡ ከርዳዳ ።
እሱ ፡ ጐልማሳ ፡ ነው ፤ እሷ ፡ ናት ፡ «ኰረዳ» ።

ዘመዶቿ ፡ ቢያይዋት ፡ ከሱ ፡ ጋር ፤ ሊቆጡ !
እናቷም ፡ አይተውት ፡ እንደ ፡ እምቧይ ፡ ሊፈርጡ ፤
ሊያንቀጠቅጣቸው ፡
ሊያንዘፈዝፋቸው ፤
ቅዠት ፡ ሊሉት ፡ እሱን ፡ ቢያዩት ፡ በሕልማቸው ፡
—ሰይጣን ፡ ሥዕሉ ፡ ሲሣል ፡ በሀገራቸው ፡
ጠጉሩም ፡ ከርዳዳ ፡ ነው ፡
ፊቱም ፡ ጥቁር ፡ ነው ።



ግን ፡ ፍቅር ፡ ይስባል ፡
ከልጓም ፡ ከዘር ።
እሱ ፡ አገናኘቸው ፡ በፈረንጅ ፡ አገር ።
ፍቅር ፡ አይቸኩልም ፡
ሰዓቱን ፡ ያውቀዋል ፤

የዘገየ ፡ ለሱ ፡ ያመሸ ፡ ይመስለዋል ።

ሦስት ፡ ቀን ፡ ሲቀራት ፡
አገሯ ፡ ልትገባ ፡
መርከብ ፡ ልትሣፈር ፡ ያቺ ፡ ጽጌ ፡ አበባ ፡
ፍቅሯን ፡ ታየዋለች ፤
ዓይታው ፡ ታለቅሳለች ፤
አጋጣሚን ፡ ረግማ ፡ ትመርቀዋለች ።
እሱም ፡ በበኩሉ ፡
መረረው ፡ ሕይወት ፤
—አለማየት ፡ ይሻል ፡ ዓይቶ ፡ ከማጣት ።

ከንፈራቸው ፡ አራት ፡
ልባቸው ፡ ሁለት ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ስድስቱ ፡ አካላት ።
ጊዜውን ፡ አጠፉት ፡ በመተያየት ፡
ሰዓቱ ፡ አጠረና ፤ ጠፉና ፡ ሌሊት ።
«ይህ ፡ ነው ፡ ፍቅር ፤ ? » አሱ
« ይህ ፡ ነው ፡ ፍቅር ? » አሉ ፤
ማመን ፡ አቃታቸው ፤
ድንገት ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ስለሠረቃቸው ።

የሚቻል ፡ ነው ፡ ለካ ፡
መሆን ፡ አንድ ፡ አካል ፤
ቁም ፡ ነገር ፡ የለውም ፡ ባይሆኑ ፡ አንድ ፡ አምሳል ።

ቁም ፡ ነገሩ ፡ አይደለም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ መንፈስ ፡
ወንዝና ፡ ተራራ ፡ ባሕርና ፡ የብስ ።
ርኅቀት ፡ ያቃርባል ፡
መቅረብ ፡ ሲያራርቅ ፤
—ከዕድላችን ፡ ጋራ ፡ እንድንታረቅ ።

ይዘመዳል ፡ ባዳ ፡
የናት ፡ ልጅ ፡ ሲከዳ ፤
ፍርድ ፡ አለ ፡ ’ሚያካፍል ፡ የሕይወትን ፡ ዕዳ ።

ሰው ፡ ሰውን ፡ ማመኑ ፡
በሰው ፡ እጅ ፡ ቢጠፋ ፤
ትንሣኤው ፡ በሰው ፡ ነው ፤ ቢለማም ፡ ቢፋፋ ።

አእምሮ ፡ ላእምሮ ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡
ኃብረው ፡ ተዋህደው ፡ ሰዓቱ ፡ ቢቀርብ ፤
ዕንባቸውን ፡ ጠጡት ፡
ሥንቃቸው ፡ ሆነና ።
ተንጠርዞ ፡ ታየ ፡ የኅዘን ፡ ደመና ።
እነሱም ፡ አወቁ ፤
መለያየት ፡ መ ጣ ፡

ተመኙ ፡ ቢሞቱ ፡ ነፍሳቸው ፡ ቢወጣ ።
« ደህና ፡ እደር» አለችው ፡
« ደህና ፡ እደሪ» አላት ፡
—ነገ ፡ አለመኖሩን ፡ ሁለቱም ፡ ሲያውቁት ።



## የሰው ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ ነው

አዳም ፡ ነው ፡ ሔዋን ።
መጽደቅም ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ መሞት ፡ መኰነን ።
ከዚህ ፡ በላይ ፡ የለም ፡ የሰማይ ፡ መንግሥት ፤
—ገዝቱኝ —አውግዙኝ — ሊቀ ፡ ጳጳሳት ።
ዘር ፡ አጠፋሁ ፡ በሉኝ ፡ እናትና ፡ አባቴ ፡
ጸጸት ፡ አምርቻለሁ ፡ ፍቅርን ፡ ከመዝራቴ ፡
—ዘር ፡ አጠፋሁ ፡ በሉኝ ፡ እናትና ፡ አባቴ ።

አንቺ ፡ ሆይ ፤ አልረሳሽ ፡
ልብ ፡ አድርጌሻለሁ ፤
ሌት ፡ ተቀን ፡ ተግቼ ፡ እጠብቅሻለሁ ።
ምጽአትሽ ፡ መች ፡ ይሆን ፡
ዓለም ፡ የሚያልፈው ፤
ሰማይና ፡ መሬት ፡ የሚሳሳመው ?
መልአክ ፡ የሚዘፍነው ፡ ቆቡን ፡ ሰይፉን ፡ ጥሎ ፡
ፍቅር ፡ የሚያብበው ፡ ዕለቱኑ ፡ በቅሎ ፡
መች ፡ ይሆን ?
መች ፡ ነው ፡ የሚወጣው ፡ ያለም ፡ ትርምስምሱ ፤
የሚለየን ፡ አጥር ፡ ቅጥር ፡ ፍርስርሱ ?
ማለት ፡ የሚቀረው ፡
መባል ፡ የሚቀረው ፡
«ይሁዲ» ፤ «አረመኔ»
ስም ፡ ጠፍቶ ፡ ’ሚበቃው ፡ «አንቺ» ዳግም ፡ «እኔ»
መች ፡ ይሆን ?

እኔ ፡ አልገረምም ፤

አንችም ፡ አይደንቅሽ ፤
ሳታዪኝ ፡ ብትሞቺ ፡
ብሞት ፡ ሳላይሽ ።
እንዲህ ፡ ባይሆንማ ፤
የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፤
ይህ ፡ ዓለም ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ መቼ ፡ ይሆን ፡ ነበር ?



## ያገር ልጅ

አካሄድሽ ፡ ይምጣ ፡
አረማመድሽ ፤
ጥርስ ፡ አገላለጥሽ ፡
ከከንፈሮችሽ ፡
ትሕትናሽ ፡ አይለይ ፡ ከቅንነትሽ ።
አንገትሽ ፡ ብርሌ ፡
ወይኒቱ ፡
ማር ፡ ነሽ ።

እቀፉኝ ፡ ቢል ፡ እንኳ ፡
ደግፉኝ ፡ አይልም ፡
ምርኩዝ ፡ የማያሻው ፡
አቋቋሙ ፡ መልካም ፡
ወጣቱ ፡ ጡትሽ ።
ጨዋታ ፡ አዘውታሪ ፡ ቀበጥ ፡ ነው ፡ ዳሌሽ ።

ተረከዘ ፡ ሎሚ ፡ ጫማ ፡ የሌለሽ ፡
ነይልኝ ፡ ያገር ፡ ልጅ ፡
አውቃለሁ ፡
አለሽ ።

## መኖር መላ አገኘ

መኖር ፡ መላ ፡ አገኘ ፡
—እንደገና ፡ ደግሞ ።
ቢሞቱም ፡ ግድ ፡ የለ ፡ መስኩ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፤
መቅረትሽን ፡ ቃኝቶ ፡
መምጣትሽን ፡ አልሞ ፡
ቢሞቱም ፡ ግድ ፡ የለ ።



## ኪስ *

የኢትዮጵያ ፡ ያገራችን ፡ ልብስ ፡
እጀጠባብ ፡ ሱሪ ፡ ኩታና ፡ ቀሚስ ፡
ኪስ ፡ የለባቸውም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፤
የሚለብሳቸውም ፡ ይተክዝ ፡ ትካዜ ።

የፈረንጆችን ፡ ልብስ ፡ ካየ ፡ ካስተዋለ ፡
ያውቀዋል ፡ መቶ ፡ ዓይነት ፡ ልዩ ፡ ኪስ ፡ እንዳለ —
የደረት ፡ ኪስ ፡ አለ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡
የዳሌ ፡ ኪስ ፡ አለ ፡ የወገብ ፡ ኪስ ፡ ደግሞ ።
«የእንደዚያም» ኪስ ፡ አለ ፡ —ለመደምደሚያው ፤
ከዚህ ፡ በጐደለ ፡ አዋቂ ፡ ይሙላው ።

ለምንድን ፡ ይረባል ፡
ለምንስ ፡ ይጠቅማል ፤ የኪስ ፡ ብዛት ፡ ማት ?
ብሎ ፡ የሚጠይቅ ፡ ካለ ፡ ምናልባት ፤
ያስቸግራል ፡ በጣም ፡ እሱን ፡ ማስረዳት ።

ኢትዮጵያዊ ፡ የጠራው ፡ አበሻ ፡
ጥሬው ፡ ያገሬ ፡ ልጅ ፡ ለመደሰት ፡ ሲሻ ፤
ምንጭ ፡ ያመሰግናል ፡ ዓባይን ፡ ሳያይ ፤
የማይዋጥ ፡ ነገር ፡ አይመስለው ፡ ሲሳይ ።

# በጠራ ጨረቃ

በጠራ ፡ ጨረቃ ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡
ዓይኖቿ ፡ እያበሩ ፡ እንደ ፡ ከዋክብት ፡
«ሳማት ፡ ሳማት » አሉት ፡ «ዕቀፍ ፡ ዕቀፋት »
አላወላወለም ፤ ወጣቱ ፡ ታዘዘ ፤
ወገቧን ፡ አንገቷን ፡ በእጅና ፡ እጁ ፡ ያዘ ፤
ከንፈሩ ፡ በረአድ ፡ ወደ ፡ አፏ ፡ ተጠጋ ።

—ምንም ፡ እንኳ ፡ ጡቷ ፡ እንደሾህ ፡ ቢዋጋ ፤
ጣቷ ፡ በመሆኑ ፡ የጉማሬ ፡ አለንጋ ፤
ጆሮው ፡ ግንዱን ፡ ሰማው ፡ በጥፊ ፡ ሲናጋ ።

በጠራ ፡ ጨረቃ ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡
ዋ ፡ ጀማሪ ፡ መሆን ፤ ዋ ፡ ተማሪነት ፤
ዋ ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፤ ዋ ፡ ምክር ፡ መስማት ።



# የወንድ ልጅ ያለህ *

የዘመኑ ፡ ወጣት ፡ ጦልጧላው ፡ ፈላስማ ፡
ልበ ፡ ጣፊያ ፡ ሁሉ ፡
ወኔው ፡ የተኛበት መንፈሰ ፡ ደካማ ፤
«ኤርፃ—ኪትን» ሰምቶ ፡ አማትቦ ፡ ጸለየ ፤
ወፎቹን ፡ አላየ ፤ ንቦቹን ፡ አላየ ፤ ዝምቦቹን ፡ አላየ ፤
ከሾላ ፡ ሥር ፡ አርፎ ፡ የሚመራመር ፡
እጅና ፡ እግሩን ፡ ታሥሯል ፡ በሸረሪት ፡ ድር ።

—«ቀይ ፡ ትሁን ፡ ቀይ ፡ ዳማ ፤
ወይ ፡ ጠይም ፡ ጥቁር ?
ዘለግ ፡ ያለች ፡ ትሁን ፡ ወይንስ ፡ አጭር ?
ከትምቡሼ ፡ ገላ ፡ ወይስ ፡ ከቀጭኔ ፡
የቷ ፡ ነች ፡ ገነቷ ፡ የቷ ፡ ነች ፡ ኩነኔ ?
ባለ ፡ ሣንቲም ፡ ትሁን ፡ ወይስ ፡ ባለ ፡ ጋሻ ?
ፈረንጅ ፡ ይሻል ፡ ይሆን ፡ ወይንስ ፡ አበሻ ?
የተማረች ፡ ትሁን ፡ ወይንስ ፡ ደንቆሮ ?
የታለችና ፡ ነው !
የለችም ። ብትኖርም ፤ ትዝለለኝ ፡ ዘንድሮ »
በማለት ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ተምሮ ፡ ተምሮ ፤
በሶ ፡ እንደጨበጠ ፡ እጆቹን ፡ አጣምሮ ።

ዱሮ ፡ በጊዜያቸው ፡
ዘንድሮ ፡ ነበሩ ፡ አምናና ፡ ካቻምና ፤
ከርሞም ፡ ዘንድሮ ፡ ነው ፡ —ወንዱ ፡ የለምና

ሱሬ ፡ የታጠቀው ፡ የዮሐንስ ፡ ቅድ ፡
ቆንጆ ፡ ዓይቶ ፡ ’ማያልፈው ፡ ጠልፎ ፡ የሚወስድ ፤
« ሮማንስ » ማያውቀው ፤ የግድ ፡ የሚወድ ፤
«ጐፈሬው ፡ ከፊቱ ፡ ያለው ፡ ከምበል ፡ ደፋ »
ጐራዴው ፡ አሽሚጣጭ ፡ ጋቢውን ፡ ያጣፋ ፤
«ሽጉጥ ፡ ነው ፡ ትራሱ ፤ የቤት ፡ ሥር ፡ ነው ፡ ልብሱ ፡
« ዞሮ ፡ ይተኩሳል ፤ አይሳሳም ፡ ለነፍሱ ፤
«አሥር ፡ ሰው ፡ ቢመጣ ፡ አልነካም ፡ ያለሱ »
ብሎ ፡ ያስዘፈነው ፡ የቴዎድሮስ ፡ አሽከር ፡
የዮሐንስ ፡ አሽከር ፡ የምኒልክ ፡ አሽከር ፡
ማተቡ ፡ ጥንካሬው ፡ ፈረሱን ፡ የሚያሥር ፡
—ሱሬ ፡ የታጠቀው ፡ ወንዱ ፡ የለምና ።

አይ ፡ ጉድ ፡ ሥልጣኔ ፤ ባሕር ፡ መሻገር !
ሱሬ ፡ የታጠቀ ፡ ወንድ ፡ ይጥፋ ፡ ባገር ?
አወይ ፡ ሥልጣኔ ፡ የገላቢጦሹ ፤
ሴቱ ፡ ሱሬ ፡ አጥልቆ ፡ ወንዶቹ ፡ ሲሸሹ . . . .

አሳዩኝ ፤ ማን ፡ አለ ፤ ከኛ ፤ የጠለፈ ፤
ራሱ ፡ ’ማያበራ ፡ ጊዜው ፡ ያላለፈ ፤
ሽበት ፡ ያልወረረው ፡ ጥርሱ ፡ ያልረገፈ ?
የለም ። ከኛ ፡ መሀል ፤ የለም ፡ የጠለፈ ፤
የጠለፈ ፡ የለም ፡ ከድግስ ፡ ያረፈ ።

ሙሽሮች ፡ ንገሩን ፡
እንዳይገባን ፡ ግራ ፡



በደረሰ ፡ ጊዜ ፤ ቢደርስ ፡ የኛም ፡ ተራ ፤
ካራሚላ ፡ ነወይ ፡ አዲሱ ፡ ሙሽራ ?
ትጣፍጣለች ፡ ወይ ፡ የማሯ ፡ ጨረቃ ፤
ያች ፡ ዳቦ ፡ ጣይልኝ ፡ ያቺ ፡ ድምቡልቦቃ ?
አስፈላጊ ፡ ነወይ ፡ ዛሬ ፡ በኛው ፡ ጊዜ ፡
ሥራ ፡ አለው ፡ ወይ ፡ በውነት ፡ አቶ ፡ አንደኛ ፡ ሚዜ ?
ግብ ፡ ግብ ፡ እንደሆን ፡
በምኒልክ ፡ ዘመን ፡ በደጉ ፡ ቀን ፡ ቀርቷል ።
መች ፡ እንዲህ !
ያን ፡ ጊዜ ፤ የሚዜው ፡ አፍንጫ ፡
ይደፈጠጥ ፡ ነበር ፡ በልጅቱ ፡ እርግጫ ።
ያን ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፡ ሴቱ ፡ ሳይቀር ፡ ወንድ ፤
እንዲህ ፡ ፈርሶ ፡ ሊቀር ፡ የሀገር ፡ ልማድ ።

ሙሽሮች ፡ ንገሩን ፤
የፍቅር ፡ አበባ ፡
ይጠወልጋል ፡ ወይ ፡ ያለ ፡ ሞዳሞዳ ?
ምንድን ፡ ይሆን ፡ ከቶ ፡ መድኃኒቱ ፡ በሉ ፡
ላሪስቶን ፤ ለፋምሺክ ፤ ለወርቅ ፡ አፍሳሽ ፡ ተክሉ ?

ንገሩን ፡ በሉና ፡ —መጋባት ፡ መነሻ ፤
መደምደሚያ ፡ አይደለም ፡ ያለም ፡ መጨረሻ ።
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ዘሩን ፡ ባይቈጥር ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —በልጽጎ ፡ ባይከብር ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ቢሄድ ፡ በሁለት ፡ እግሩ ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ወይ ፡ በኩርኩሩ ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —መኪናው ፡ ብትሆን ፡

ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ያችው ፡ ፎክስቫገን
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ካኪ ፡ ቢሆን ፡ ልብሱ ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —አብዱል ፡ ቢባል ፡ እሱ ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ከልጓም ፡ ከዘር ፡
ንገሩን ፡ በሉና ፡ —ይሰባል ፡ ፍቅር ።

—ኪሩብ ፡ ነው ፡ ሱራፌ ፤

ክንፋዊ ፡ ነው ፡ ፍቅር ።

ንገሩን ፡ በሉና ፤ አይበለን ፡ ቅር ፡ ቅር ፤
—በራካቢ.ኜሪ ፡ አይያዝም ፡ ፍቅር ።

ስትሉ ፡ እንሰማችሁ ፡ —ሼብሮሌት፤ ዶዥ ፤ ይቅር ፤
አቡጀዲድ ፡ ይልበስ ፡ ካኪውን ፡ ተገፎ ፤
ፍቅር ፡ ጣዩ ፡ ይሞቃል ፡ ሲተኙ ፡ ተቃቅፎ ።

በሉና ፡ እመኑልን ፡ —እርግጥ ፡ ነው ፡ እውነት ፡
ፍቅር ፡ በሽታ ፡ ነው ፡ የደስታ ፡ ዕብደት ።
በሉን ፡ —ሞት ፡ ይሻላል ፡ ወዶ ፡ ከመጥላት ።



## በገላጋይ *

### ወጣት

«ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ አግኝቼ ፡ ወዲያው ፡ ከሙውደዶ ፤
ምን ፡ ምን ፡ አለው ? አለች ፡ —ቁርጥ ፡ አለ ፡ ሆዶ ።
ምን ፡ ምን ፡ አለው ? አለች ፤ ምንድነው ፡ ሳትል ።
ሣሎን ፡ አለው ? አለች ፤ ራዲዮን ፡ በዚያ ፡ ላይ ?
ቴሌቪዥን ፡ አለች ፡ ሲኒማ ፡ ብታይ ።
ፎክስቫገን ፡ አለች ፡ ስድብ ፡ ነው ፡ ውርደት ፤
—ፖንቲያክ ፡ ነው ፡ ሼቭሮሌት ፡ መኪና ፡ ማለት ።
ቅዳሜ ፡ ገፈርሣን ፡ ሰንዳፋን ፡ እሑድ ፡
የማይረግጠው ፡ ታዲያ ፡ ይባላል ፡ ወይ ፡ ወንድ ?
ክስር ፡ ብሎ ፡ ከስሮ ፡ ድግስ ፡ ካልደገሰ ፡
የሴት ፡ ልጅ ፡ ክብርና ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ረከሰ !

ማን ፡ በነገረልኝ ፡ ማን ፡ በነገራቸው ?
እዝጌር ፡ ያሳያችሁ ፤ እዝጌር ፡ ያሳያቸው ፡
የፍቅርን ፡ ትርጋሜ ።
ፍቺው ፡ አልጠፋቸው !»

### ሺክ—ልጅ

« መኪና ፡ አለች ፡ ይላል ፡ —ይመክነውና ።
ያን ፡ የሐር ፡ ማተቡን ፡ ክራባት ፡ ያሥርና ፡
በሱፍ ፡ ሙሉ ፡ ልብሱ ፡ ይሽቀረቀርና ፡
ያሜሪካን « ቀስቶ » ሸሚዝ ፡ ያጠልቅና ፡
የጆን ፡ዋይትን ፡ ጫማ ፤ ሹሉን ፤ ይሰካና ፤
ልቡ ፡ ውልቅ ፡ ብሏል ፡ ተሠለጠነና ።

ይህ ፡ ግድርድር ፡ ጅግራ ፤ ይህ ፡ ዝንጉርጉር ፡ ቆቅ ፤
ፍቅርን ፡ በምን ፡ ይወቅ ፡ ልቡ ፡ እንዲህ ፡ ሲወልቅ ?
ይህ ፡ ቀብራራ ፡ ያንኪ ፤ ኮፍናና ፡ እንግሊዝ ፡
ጡት ፡ ባት ፡ ባየ ፡ ቁጥር ፡ ይገኛል ፡ ሲፈዝ ፤
ሚስቱን ፡ አርባ ፡ ሲገርፍ ፤ ሲሰክር ፤ ሲጠጣ ፡
የትም ፡ ውሎ ፡ አምሽቶ ፡ ወይ ፡ አድሮ ፡ ሲመጣ ፤
ደሞዙን ፡ አካፍሎ ፡ ለያራዳው ፡ ሴት ፡
ይገዛበት ፡ ሲያጣ ፡ ለልጁ ፡ ወተት ።
ኧረ ፡ ስንቱን ፡ ስንቱን ፤ ስንቱን ፡ ልንገራችሁ !
እዝጌር ፡ ያሳያቸው ፤ እግዜር ፡ ያሳያችሁ ፡
የፍቅርን ፡ ትርጓሜ ።
ፍቺው ፡ አልጠፋችሁ ! »

## ሽማግሌ

« ያስታራቂ ፡ ያለህ ፤ እረ ፡ በገላጋይ !
ሽማግሌን ፡ ስሙት ፤ አንተም ፡ ተው ፤ አንቺም ፡ ተይ ።
እቴ ፡ አንችም ፡ አይደለሽ ፤ ዘመኑ ፡ ነው ፡ ቀኑ ፤
ወንድም ፡ አንት ፡ አይደለህ ፤ ጊዜው ፡ ነው ፡ ዘመኑ ።

አንዲት ፡ ቅጠል ፡ ወድቃ ፡ ከሁለት ፡ ዕንጨቶች ፡
ትሆነውን ፡ ስታው ፡ ትጨነቃለች ።
ፈረንጅ ፡ አይደላችሁ —በድግሥ ፡ ክሠሩ ፤
አበሻ ፡ አይደላችሁ—ሳታገቡ ፡ አፍቅሩ ።
በኛው ፡ ዘመንማ ፡
መግባባቱም ፡ ሳለ ፤
ትዳር ፡ ቀደመና ፡ ፍቅር ፡ ተከተለ ።



እናትና ፡ አባትሽ ፡ በፍቅር ፡ አረጁ ፡
አባትና ፡ እናትህ ፡ በፍቅር ፡ አረጁ ፤
በገዛ ፡ እጁ ፡ አበጀ ፡ ሠንሠለቱን ፡ ልጁ ።

« እንዴት ፡ አገባለሁ ፡ ሳንተዋወቅ ? »
—ይቻለው ፡ ይመስል ፡ ሰው ፡ እራሱን ፡ ሊያውቅ !

ሚስቱን ፡ እንደ ፡ ቦርሳ ፡ አንግቶ ፡ ካልዞረ ፡
እሷን ፡ እንደ ፡ ጋሻው ፡ አንግቦ ፡ ካልዞረ ፡
ደሞ ፡ አብሯት ፡ ካልዋለ ፡ አብሯት ፡ እያደረ ፤
አይባልም ፡ አሉኝ ፡ ወጣቱ ፡ ተማረ ።
እኔ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ አልታጭ ፡ አላጭ ፤
ስትግተለተል ፡ ኑር ፡ እስክትሰላች !

በፈረንጆች ፡ አሉኝ ፡ በሠለጠኑት ፡
በቀን ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ትሳማለች ፡ ሚስት ።
ያገር ፡ ልማድ ፡ ባይሆን ፡ ይህ ፡ ነበር ፡ ዕብደት ።
ዕብደትም ፡ ከሆነ ፡ የኛው ፡ ዕብደት ፡ ይብቃን ።
ቋንቋ ፡ ተማራችሁ ፤
ላለመስማማት ።

የለም ፡ የለም ፡ የለም ፤ የለውም ፡ አልኳችሁ ፡
መፍትሔ ፡ መድኃኒት ፡ ለዚህ ፡ በሽታችሁ ።
መስሏችሁ ፡ ለናንተ ፤ ይገኛል ፡ ስትሉ ፤
አንድ ፡ አይትረፋችሁ—በሉ ፡ ሥር ፡ ንቀሉ ።
ጊዜ ፡ ያመጣውን ፡ እስኪወስደው ፡ ጊዜ ፡
ጊዜ ፡ የሾመውን ፡ እስኪሽረው ፡ ጊዜ ፡
ዕጣችሁ ፡ ነውና ፡ ብስጭት ፡ ትካዜ ፤

ጊዜ ፡ ያመጣውን ፡ እስኪወስደው ፡ ጊዜ ።

«ጊዜ፡ እጅ ፡ እግር ፡ አለው ፡ አእምሮ ፡ አለው ፡ ጊዜ ?
«ጊዜ ፡ ያደርገዋል ፡ ማለትህ ፡ ነው ፡ ከንቱ »
ሳትሉኝ ፡ አትቀሩም ፡ ያወቃችሁቱ ።

ላንደጊዜ ፡ እንስማማ ፡
ግን ፡ አትፍረዱብኝ ፡
አዳም ፡ በዘመኑ ፡ ሰው ፡ ሲያጣ ፤ ሳያገኝ ፤
ተስፋችን ፡ ትንፋሿ ፡ እንዳትቋረጥ ፤
ይገደዳል ፡ ሥጋ ፡ መንፈስ ፡ እንዲሰጥ ፡
እንዲሰጥ ፡ አእምሮ ፡ አስተውሎ ፡ ሕሊና ፡
ረቂቅ ፡ አስተያየት ፡ ብሩሁን ፡ ልቦና ፤
ሥጋ ፡ ለለበሰው ፡ በስዊስ ፡ ሰዓት ፡
እንደ ፡ ጊዜ ፡ ላለው ፡ ያእምሮ ፡ ፍጥረት »



# እናትና ልጅ *

(የሰው ፡ ልጅ ፡ አእምሮ ፡ እየተራቀቀ ፡
ኃላፊን ፡ መጻኢን ፡ ዐወቀ ፡ ጠየቀ ።
የአስትሮኖሚ ፡ ሲፈታ ፡ ራዕዩ —
ኮከብ ፡ ቈጣሪዎች ፡ አንዱን ፡ ኮከብ ፡ ሲያዩ ፤
ላንድ ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ ብቻ ፡ ተመልክተው ፡
የመንገዱን ፡ መሥመር ፡ ያውቁታል ፡ ለይተው ።
« በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ዘመን ፡ በእንዲህ ፡ ያል ፡ ዓመት ፡
« በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ወር ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ዕለት ፤
« በዚህ ፡ ያህል ፡ ሰዓት ፡ ከእንደዚህ ፡ ደቂቃ . . »
ያሉት ፡ ቃል ፡ ይደርሳል ፡ እንደ ፡ ላኩት ፡ ዕቃ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪዎች ፡ ከሚያምኑት ፡ እምነት ፡
አንዱ ፤ የጨረቃ ፡ ከምድር ፡ መገኘት ፤
ይፈልጋልና ፡ መታወቅ ፡ በጣሙ ፡
ጆሮዋችሁን ፡ አስሉ ፤ ይህን ፡ ተረት ፡ ስሙ ፡—

ምድራችን ፡ እንደ ፡ እንዝርት ፡ ስትሽከረከር ፡
ፀሐይ ፡ አሳብዳት ፡ ያዙሪት ፡ ስትዞር ፡
በጣም ፡ በረታና ፡ « ሴንትሪፉጋል—ፎርስ »
የነበረው ፡ ቅርጿ ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡
ሞለል - ሞለል - ሞለል ፡ ሞለ-ለለ ፡ ሲል ፡
መድቦልቦሉ ፡ ቀርቶ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ዕንቁላል ።
ሞላላ ፡ እንደ ፡ ዕንቁላል ፡ መች ፡ ሆኖ ፡ ሊቀር ?
በሾላላው ፡ ወገን ፡ ይራዘም ፡ ጀመር ።

ዓመታትም ፡ አልፈው ፡ ከዘመናት ፡ ጋራ ፡
ወዲያው ፡ ደረሰና ፡ የታምራት ፡ ተራ ፤
በሾላላው ፡ በኩል ፡ የነበረው ፡ ጫፍ ፡
ተጕርዶ ፡ በረረ ፡ ዘላለም ፡ ላያርፍ ።

ጕራዳና ፡ ጉራጅ ፡ ያለማችን ፡ ጣቃ ፡
አንዱ ፡ መሬት ፡ ሆነ ፡ አንደኛው ፡ ጨረቃ ።
—ምድራችን ፡ ናትና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነድ ፡
ያያት ፡ ሰውም ፡ የለ ፡ ጨረቃን ፡ ስትወልድ ።)

<u>ጨረቃ</u> ፤— « ወዝ ፡ የለሽ ፡ አመዳም ፡
ነፍስ ፡ ቢስ ፡ ደረቅ ፡
እያለ ፡ ሲሰድበኝ ፡ ያየኝ ፡ ሰው ፡ ከሩቅ ፤
ጀሮዬን ፡ ሰለቸው ፡ አንገፈገፈኝ ፡
የልደቴን ፡ ሰዓት ፡ ቀን ፡ አስረገመኝ ፤
ምን ፡ በደልኩ ፡ እናቴ ፤ ለምን ፡ ወለድሽኝ ! »

<u>መሬት</u> ፡— « ይህን ፡ መናገርሽ ፡
ልጄ ፡ ሆይ ፤ ጡር ፡ ነው ።
ያንቺ ፡ ኑሮ ፡ ባለም ፤ የኔን ፡ ባየሽው !
—የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚሉት ፡ የኔ ፡ ራስ ፡ ቅማል ፡
በስምንተኛው ፡ ሺ ፡ ነገር ፡ አምጥቷል ።

በእርሻ ፡ መኪና ፡ ሥጋዬን ፡ ተልትሎ ፡
ዳግም ፡ የኔኑ ፡ አጥንት ፡ « ደንጊያ ፤ ብረት » ብሎ ፡
ለማውጣት ፡ እያለ ፡ ይሠረሥረኛል ፤
ደሞ ፡ « ዕንጨት » እያለ ፡ ጠጉሬን ፡ ይላጨኛል ።



ለዚሁ ፡ ሲገርመኝ ፡
በሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡
አሥራራት ፡ ታላቁ ፡ ጦርነት ፡ ተነሥቶ ፤
የሰው ፡ ልጅ ፡ እስበሱ ፡ ሊፋጅ ፡ ነው ፡ ስል ፤
ለራሴም ፡ ተረፈኝ ፡ የቈላ ፡ ቁስል ።

ካናል—ስዌዝና ፡ ፓናማ—ካናል ፡
ሲሠሩስ ፡ ያየሁት ፡ ሥቃይ ፡ ምን ፡ ያህል ፡
ይመስልሻል ፡ ልጄ ?
እንደዚያም ፡ ብሆን ፡
እግዚአብሔርን ፡ ስለው ፡ ነበር ፡ ተመስገን ።

ከቅማሉ ፡ ሁሉ ፡ በራሴ ፡ ካለው ፡
የሚበላኝ ፡ በጣም ፡ ነጭ ፡ ነጩ ፡ ነው ።
የተበላው ፡ ጐኔ ፡ አውሮፓ ፡ ይባላል ፤
አሜሪካም ፡ ደሞ ፡ መባላት ፡ ጀምሯል ።
አፍሪቃና፡ እስያ ፡ እንዲያ ፡ ቢሆኑማ ፡
ምን ፡ ተረፍኩኝ ፡ ብለሽ ፡ አካሌ ፡ እየደማ ?

ባፍሪቃ ፡ በእስያስ ፡ ያሉት ፡ ቅማሎች ፡
መች ፡ ነቅተው ፡ ሊበሉኝ ?
ሁሉ ፡ ዕንቅልፋሞች !
ምን ፡ ይሆናል ፡ ግና ፡ ነጫጮቹ ፡ እያሉ ፤
—ደኅና ፡ የተኙትን ፡ ይቀሰቅሳሉ ።
ጥቋቁሮቹና ፡ ደሞ ፡ ብጫዎቹ ፡
ተነሥተው ፡ ያዩና ፡ ሲቀብጡ ፡ ነጮቹ ፤
እነሱም ፡ እንደኒያ ፡ ካልቀበጥን ፡ እያሉ ፤
እኔኑ ፡ ለመጉዳት ፡ ይሽቀዳደማሉ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ በደል ፡
ተቈጥሮ ፡ ተሠፍሮ ፡ ተነግሮ ፡ ያልቃል ?

በሺ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዘጠኝ ፡
እንዳውሮፓ ፡ ቁጥር ፡
« ፀሐይ ፡ ካልሞቀኝ »
ብሎ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ቢያነሣ ፡ ሂትለር ፤
ሰው ፡ በመፋጀቱ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ነበር ።
ጦርነታቸውን ፡ መች ፡ ወድጄው ፡ ነው ?
የቦምቡ ፡ የመድፉ ፡ መዓት ፡ ምግቤ ፡ ነው ።
ሆኖም ፡ በጀግንነት ፡ ያለቀውን ፡ ሰው ፡
ስላየሁ ፤ ለሂትለር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስጠው ።

ያውሮፓው ፡ ጦርነት ፡ ባለቀብኝ ፡ ጊዜ ፡
ጃፓን ፡ ስለ ፡ ቀረኝ ፡ ባልተከዝ ፡ ትካዜ ፤
ለምን ፡ ደስ ፡ ይበላት ፡ ብለው ፡ ያለ ፡ ደምብ ፡
ካሳረሩኝ ፡ ወዲህ ፡ በአቶሚክ ፡ ቦምብ ፤
እተርፋለሁ ፡ ማለት ፡ የሰው ፡ ዘር ፡ ያልቅና ፡
የሕልም ፡ እንጀራ ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡ ቃል ፡ ነውና ፤
ይሻለኛል ፡ አልኩኝ ፡ ወዲያ ፡ አልፎ ፡ ባርፈው ፡
ነዶ ፡ ሆዶ ፤ ገምኖ ፡ ሆዶ ፡
እንዲህ ፡ ከምኖረው ።

መለስ ፡ ብዬ ፡ ደሞ ፡ ታሪኬን ፡ ሳየው ፡
«የኖኅ ፡ ዘመን ፡ ዛሬ ፡ በሆነ ፡ ምነው ! »
እንዳልኩኝ ፤ የጌታን ፡ ዳግማዊ ፡ ምጽአቱን ፡
ናፍቄው ፡ እላለሁ ፡ « ጊዜው ፡ መቼ ፡ ይሆን ? »

—ሳይንስ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የሚሰብኩትማ ፡
አይነገር ፡ ወዲያ ፡ ይቅር ፡ አይሰማ !



የማይሳደቡስ ፡ ሰላማውያን ፡
ያበሻ ፡ ሊቃውንት ፡ ወዳጆች ፡ አሉን ።
እኔንም ፡ ዘዋሪ ፡
አንችንም ፡ ዘዋሪ ፡
እያለ ፡ ሲሰድበን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍጥረት ፤
ካፋቸው ፡ ያልወጣ ፡ እንዲህ ፡ ያል ፡ ቅሌት ።
እንደሚሉትማ ፡ ቢሆንልኝ ፡ እሺ ፤
—ታልፊያለሽ ፡ ይሉኛል ፡ በስምንተኛው ፡ ሺ ።

ልምከርሽ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፤ ልንገርሽ ፡ ስሚኝ ፡-
እናትሽን ፡ ከማለት ፡ ለምን ፡ ወለድሽኝ ፤
ተሰደብኩኝ ፡ ብለሽ ፡ ከምታማርሪ ፤
ካንችም ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የመጣ ፡ ለት ፡ ፍሪ ።

## ሞኚት ተላሊት

ጅግራ ፡ ሊይዝ ፡ ሄዶ ፡ ፈረንጅ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡
ድፍቱን ፡ አጥምዶ ፡ ካንዱ ፡ ቈንጥር ፡ ሥር ፡
ከያዘው ፡ ከረጢት ፡ ጥሬ ፡ ጨበጠና ፡
ድፍቱ ፡ ሥር ፡ በርከት ፡ አርጎ ፡ አፈሰሰና ፡
በወጥመዱ ፡ ዙሪያ ፡ ጥሬ ፡ ፈነጣጥቆ ፡
ወደ ፡ ጢሻው ፡ ገባ ፡ እንዲያይ ፡ ተደብቆ ።

ከዚያ ፡ ስፍራም ፡ ደርሳ ፡ እነሆ ፡ አንድ ፡ ጅግራ ፡
አየችና ፡ ቆማ ፡ ወጥመዱን ፡ ተኩራ ፤
ጉዞዋን ፡ ቀጠለች ፡ በልቧ ፡ እንዲህ ፡ ብላ —
« ወጥመድም ፡ አልገባ ። በቆሎም ፡ አልበላ »

አጥማጅ ፡ በበኩሉ ፡ ነበር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡-
« እሰይ ! ገባችልኝ ፤ ማረካት ፡ በቆሎ »
ግን ፡ ወጥመዱን ፡ ዘላ ፡ ስትሄድ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
ባለመታደሉ ፡ ተከዘ ፡ ትካዜ ።

ሌላ ፡ ጅግራ ፡ ደግሞም ፡ ብትመጣ ፡ ሁለተኛ ፡
« ይህ ፡ ጥሬ ፡ በቆሎ ፡ ይጥማል ፡ ምንኛ ! »
ብላ ፡ እያጣጣመች ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ በልታ ፡
ስትጨርስ ፡ ሄደች ፡ መንገዷን ፡ አቃንታ ።

ይህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ባለ ፡ ወጥመድ ፡
ይቁነጠነጥ ፡ ጀመር ፡ ይቃጠል ፡ ይነድ ፡-
« እኔስ ፡ ለበቆሎ ፡ ስትስገበገብ ፡



« እወጥመዴ ፡ ገብታ ፡ ልትሆነኝ ፡ ምግብ ፡
« ነው ፡ ብዬ ፡ ነበረ ፤ የሷማ ፡ ውለታ ፡
« መክዳት ፡ ብቻ ፡ ሆነ ፡ እህሌን ፡ በልታ ፡ በልታ !
« ብነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቤቴ ፡ ላደን ፡
« በጠማማ ፡ ኮከብ ፡ በጐደሎ ፡ ቀን . . .
« ሆኖም ፡ በወንጌል ፡ ቃል ፡ በትንሣኤ ፡ ሙታን ፡
« በመጻኢው ፡ ሕይወት ፡ ያመነ ፡ ክርስቲያን ፡
« ምንም ፡ ቢደርስበት ፡ ተስፋ ፡ አይቈርጥምና ፡
« ሦስተኛ ፡ ብትመጣ ፡ ላስተውል ፡ እንደ ፡ ገና »

ሦስተኛዋ ፡ ጅግራ ፡ እንደ ፡ ደረሰች ፡
በወጥመዱ ፡ ፍሬ ፡ ተዘርግፎ ፡ አየች ።
ድፍቱን ፡ ሳትገባም ፡ ከበራፉ ፡ ሆና ፡
ታሰላስል ፡ ጀመር ፡ ወደፊት ፡ ለገና ፡
የምታገኘውን ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡
ገብታ ፡ ከወጥመዱ ፡ ብትደነቀር ።
እሷም ፡ በሐሳቧ ፡ እንደዚህ ፡ አለች ፤—
« ምን ፡ ደጎቹ ፡ ናቸው ፡ እኒህ ፡ አጥማጆች !
« ካለንበት ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ በማባበል ፡
« እቤታቸው ፡ ወስደው ፡ ያቀማጥሉናል—

« አሁን ፡ ከድፍቱ ፡ ገብቼ ፡ ብያዝ ፡
« ዐውቃለሁ ፡ ይህ ፡ ፈረንጅ ፡ እንዲፈነጥዝ ፤
« እሠፈሩ ፡ ወስዶ ፡ በሠራልኝ ፡ ቤት ፡
« እንደሚያስቀምጠኝ ፡ በሽቦ ፡ ወንፊት ፤
« እንደሚመግበኝ ፡ በቆሎና ፡ ስንዴ ፡
« እንደ ፡ እርጥብ ፡ ስልቻ ፡ እስኪወጠር ፡ ሆዴ ።

« ከሰባሁ ፡ በኋላም ፡ እንዲያ ፡ ተቀልቤ ፡
« ይታቀፈኝና ፡ ቱር ፡ ቱር ፡ ሲል ፡ ልቤ ፡
« ሳብ ፡ ሳብ ፡ አንገቴን ፡ ቄልመም ፡ አድርጎኝ ፡
« ላባዎቼን ፡ ነጭቶ ፡ በሙቅ ፡ ውኃ ፡ አጥቦኝ ፤
« በሰታቴ ፡ ቅቤ ፡ እንደሚያዋኘኝ ።
« የት ፡ ይገኛል ፡ አሁን ፡ ያለኔ ፡ በቀር ፡

« መዋኘት ፡ የቻለ ፡ በቅቤ ፡ ባሕር ?
« በበሰልኩም ፡ ጊዜ ፤ ወተት ፡ በመሰለ ፡

« በሸክላ ፡ ሣህን ፡ ላይ ፡ እያንከባለለ ።
« እየመታተረ ፡ ባፉ ፡ ካስገባኝ ፡
« በሆዱ ፡ ያለውን ፡ የት ፡ ሊደብቀኝ ?
« አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አምሳል ፡ ከሆንኩት ፡ በኋላ ፡
« ባለሟልነቴ ፡ ምን ፡ ይጠየቃላ! »

ይህንን ፡ ተናግራ ፡ አፍታ ፡ እንኳን ፡ ሳትቈይ ፡
ዘላ ፡ ጥልቅ ፡ አለች ፡ እመት ፡ ጅግራ ፡ ሆይ ።
ስትነበንበው ፡ ረጅሙን ፡ ድርሰት ፡
ዘንግታ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሞኚት ፡ ተላሊት ።



# ሕንደኬ

# ጠላና ሙዚቃ

ምን ፡ ነካኝ ? እላለሁ ፡ የታመምኩት ፡ ሰው ፡
የከበበኝ ፡ ሁሉ ፡ ማማሩ ፡ ምነው ?
ጆሮዬም ፡ መስማቱ ፡ ዛፎች ፡ ሲዘምሩ ፡
ዓይኔስ ፡ የሚያርፍበት ፡ ያለመቈርቈሩ ፡
አለመጐርበጡ ፡
አለመቧጠጡ ፤
ሲጃራው ፡ ትምባሆው ፡ እንኳ ፡ መጣፈጡ ።

የግጥም ፡ መጽሐፍ ፡ ሳነብ ፡ አነማና ፡
ራሴው ፡ እገጥማለሁ ፡ ያሰብኩት ፡ ቀረና ።
ይህ ፡ አያስቈጣኝም ፡
ነፃነት ፡ ይኑር ፤
ሐሳብ ፡ ክንፍ ፡ አብቅሎ ፡ ዓለሙን ፡ ይዞር ፤
ልቤ ፡ ይፈንጭና ፡ ይፈንድቅ ፡ ይብረር !

ግን ፡ አእምሮ ፡ አልተኛም ።
ምን ፡ ይሆን ፡ እላለሁ ፡ የዚህ ፡ ምክንያቱ ?
—ሶቅራጥስ ፤ አፍላጦን ፤ እዝጌር ፡ ይይላችሁ ፤
ነፍስህን ፡ አይማረው ፡ ጥንታዊ ፡ ግሪክ ፤
አንተ ፡ ነህ ፡ ይሉኛል ፡ ይህን ፡ ያስተማርከ ፡
ባልነበሩበቱ ፡ የጻፉት ፡ ታሪክ ።

አንቺ ፡ ትሆኝ ፡ ብለሽ ፡ የማስብሽ ፡ ልጅ ፡
ይህን ፡ የሠራሽኝ ፡ ወይስ ፡ ጠላ ፡ ጠጅ ?



ወይስ ፡ ሙዚቃው ፡ ነው ፡ የወዘወዘኝ ፡
ከትካዜ ፡ ዕንቅልፌ ፡ የቀሰቀሰኝ ?
—የታለ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ብስጭት ፡ ያ ፡ ጭንቅ ፤
ያ ፡ ኀዘን ፤ ንዴቱ ፤ ያ ፡ ልወቅ ፡ ልወቅ ?

ምነው ፡ ለሰለሰኝ ፡ ያጠለቅሁት ፡ ማቅ ?
ማነው ፡ ቊሮንጮዬን ፡ የቀማኝ ፡ ለማኝ ?
ሸክሙን ፡ ማነው ፡ ኩሊው ፡ ያቀለለልኝ ?

ሳትሆን ፡ ትቀር ፡ ብለሽ ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ አላፊ ፡
ሕይወት ፡ እሷ ፡ ራሷ ፤ ያች ፡ አልሚ ፤ ያች ፡ አጥፊ ፤
ሙዚቃ ፡ ጠላ ፡ አንቺ ፡ ያላችሁት ፡ በእጅዋ ፡
—ኮሶና ፡ ትርንጎ ፡ ይበቅላል ፡ ከደጅዋ —
ለማስተማር ፡ ብላ ፡ ሰውን ፤ ላይማር ፤
ምን ፡ ቢራቀቅና ፡ ምን ፡ ቢመሳጠር ፡
ፍልስፍናው ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ እንዲያውቅ ፤
ሕይወትን ፡ ለመርገም ፡
ወይ ፡ ለመመረቅ ፡
እንደማይፈቅድለት ፡ ያለበት ፡ ሁኔታ ፡-
ከራሱ ፡ ተሟግቶ ፡ ራሱ ፡ እንዳይረታ ?

## ተጣልተን ተኳርፈን

ተጣልተን ፡ ተኳርፈን ፡
ተኳርፈን ፡ ተቋርጠን ፡
« ሴጣን ፡ ነህ » ብለሽኝ ፡
« ሴት ፡ አይረባም፤» ብዬ ፡
እንጒራጒራለሁ ፡ አፍዝዞኝ ፡ ሥቃዬ ፡—
« አንቺ ፡ ልጅ ፡ አንቺ ፡ ልጅ ፡ አንቺ ፡ ልጅ ፡ አንቺዬ !»



## ሞትና መለየት

ምነው ፡ ክንዴ ፡ ራስ ፤
አንቺን ፡ ባንተራስ ?
ተንሳፍል ፡ ጉልላት ፡ ደክሞት ፡ መዋኘቱ ፤
ማን ፡ ይባላል ፡ ወንዙ ፡ ፈሳሹ ፡ ኸረቱ ?
ተናገሪ ፡ እባክሽ ፡ አንች ፡ ዓይናማይቱ !
—ወይንም ፡ ዝፈኚ ፤ እንጒራጒሪ ፤ በይ ፤
« ሞትና ፡ መለየት ፡ አንድ ፡ አይደለም ፡ ወይ ... »
በይ ፡ አብረን ፡ እንዝፈን ፤ ድምፃችን ፡ ይስማማ ፡
ወዳጅ ፡ ጐረቤቱ ፡ ዘመዱም ፡ ሳይሰማ ፤
የጎዘንን ፡ ዘፈን ፡ የትካዜን ፡ ዜማ ።
ልብ ፡ ይምታ ፡ ከበሮ ፡ ዓይናችን ፡ ሲያወርድ ፤
ከንፈራችን ፡ ይግጠም ፡ በ«ውድ»ና ፡ «ግድ »
ውድ ፡ አንች ፡ ነሽና ፤ ግድም ፡ መለየት ፤
ይኸውልሽ ፡ ዓለም ፡ አዱኛ ፡ ሕይወት ።

መሄዴ ፡ ነውና ፡ አየሩን ፡ በርሬ ፡
መሄዴ ፡ ነውና ፡ ባሕሩን ፡ መሻገሬ ፡
ደኅና ፡ ሁኚ ፡ እንግዲህ ፡ አንች ፡ አንድዬ ፡ ፍቅሬ ።
እንዳይሟሟ ፡ ልቤ ፡
እንዳይባባ ፡ ሆዴ ፡
ፎቶግራፍሽን ፡ ስጪው ፡ ለደረቴ ፡ ኪስ ፤
እመለስ ፡ ይሆናል ፡ ወይ ፡ አልመለስ ።

ሰማይ ፡ ሰማያዊ ፡ መሬት ፡ ዝንጉርጉር ፡
ሉዓላዊው ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ያፈር ፡ ክምር ፡

ሲጫወቱ ፡ ልጆች ፡ የሚከምሩት ፤
የኰራው ፡ ገመገም ፡ ሲነጠፍ ፡ ከምድር ፡
አውራ ፡ ጐዳና ፡ ነው ፡ የሽረሪት ፡ ድር ፡
ዐባይ ፡ መጫኛ ፡ ነው ፡ ጣናን ፡ ሲቋጠር ፡
ግዮንም ፡ ዘንዶ ፡ ነው ፡ ተቈላሞ ፡ የተኛ ፡
—እንደማያጅበው ፡ መቶ ፡ ፈረሰኛ —
ሰው ፡ ከቁጫጭ ፡ ያንሳል ፡ ካሻንጉሊት ፡ ቤቱ ፤
በጉም ፡ ጭላንጭል ፡ ነው ፡ ይህም ፡ መታየቱ !

ከዚህ ፡ በላይ ፡ አለ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማይ ።
አምላክ ፡ ተቀምጦ ፡ ከላይኛው ፡ ላይ ፤
ካላየልኝ ፡ ይላል ፡ የኔን ፡ ኩላሊት ፡
የሰው ፡ ልጅ ፡ ከብት ፡ ነው ፡ የሐሙስ ፡ ፍጥረት ።



# ሕንደኬ *

ዕንባው ፡ ኰለል ፡ አለ ፡ ጆርባዬ ፡ ሲያለቅስ ፡
ካልካታ ፡ ላይ ፡ ሞቼ — እንዲያ ፡ ተርፎ ፡ ነፍስ ።
ገደለኝ ፡ አድሞ ፡ ደረጃ ፡ አዳሪው ፡
በመንፈስ ፡ አረገኝ ፡ የሥጋ ፡ ቢጤው ፤
ሽምብራ ፡ ፈሰሰ ፡ የማተቤ ፡ ወርቅ ፡
ዶቃው ፡ ደቀቀልሽ ፡ ካንገቴ ፡ ሲወድቅ ፤
—አመድ ፡ ሆና ፡ ትቢያ ፡ አይነቅዝም ፡ ያልኩት —
እፍ ፡ አልኩት ፤ በነነ ፤ ወርቀ ፡ ሃይማኖት ።
ነበርኩና ፡ ባዩ ፡ በኢትዮጵያ ፡
« ሰው ፡ ሊማር ፡ ይችላል ፡ ከሌሎች ፡ አርአያ »
የምል ፡ ነበርኩና ፡ « ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡
ሊታረም ፡ ይችላል ፡ ሊታረቅ ፡ ተፈጥሮ »

ሕንደኬ ፡ ካሺኛ ፤
ምትኩን ፡ ስጪኛ !
ካሺኝ ፡ በቪኖባ ፡ በበሀቬ ፡ እምነት ፡
ተስፉ ፡ ሁሉ ፡ ሲሞት ፡ ተስፋው ፡ በማይሞት ።
ስጭኝ ፡ የኔ ፡ ይሁን ፤ አንችም ፡ ተጋበዢ ፤
የማለቱ ፡ አለኝታ — ልጆችሽን ፡ ገዢ ፡
የሆነው ፡ ልማዱ ፡ ወጉ ፡ ባህሉ ፡ እምነቱ ፡
እንደ ፡ መበርከቱ ፡ እንደ ፡ መበርታቱ ፡
እንደ ፡ ልዩነቱ ፡ እንደ ፡ ዕውርነቱ ፡
ሥሩና ፡ ጅማቱ ፡ ጠልቆ ፡ እንደ ፡ መጥናቱ ፤
ሕይወቱን ፡ አማጥኖ ፡

በሱ ፡ ሊተዳደር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከቻለ —
ቢለዋወጥሳ ?
ተስፋ ፡ አለ ። ተስፋ ፡ አለ ።



## ማናሊ *

ማናለ ፡ ማናሊ ፡ አንቺን ፡ የመሰለ ?
ወንዝሽ ፡ አንጐርጓሪ ፡ ውኃው ፡ የጠለለ ፡
ዛፍሽ ፡ ያልበቀለ ፡ ወይ ፡ ያልተተከለ ፡
እንዲያው—እንደዚሁ—ብቻ ፡ እንዲሁ—ያለ ።

ደንጊያ ፡ ተንተርሶ ፡ በጋሮችሽ ፡ ጥላ ፡
እየተጐነጨ ፡ ያየርሽን ፡ ጠላ ፡
ሲገርመው ፡ መዝፈኑ ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ሌላ ፤
መኖር ፡ የመረረው ፡ ዓለምን ፡ የጠላ ፤

ገደሉ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አንድ ፡ የጥድ ፡ ግልገል ፡
—ምን ፡ ገዶት ! አያውቀው ፡ የሱን ፡ መታደል ፤
አልተመለመለ ፡ ለምሶሶ ፡ አልታጨ—
ጆሮቹን ፡ ሲቀስር ፡ ነፋስ ፡ ስላፏጨ ፤
ታዝቦ ፡ ተራራ ፡ ያ ፡ ሸበቶ—ራሱ ፡
ቢስቅ ፡ ያምርበታል ፡
በረዶ ፡ ነው ፡ ጥርሱ ።

## ቦምቤይ *

ፖሊስ ፡ አቆመና ፡ ጠየቀን ፡ በቦምቤ ፡
«ላነፍንፈው ፡ እስቲ ፡ አፍህን ፡ ቀርቤ .......
«ትሸታለህ ፡ ቪኖ ፡ ቪኖ ፡ ሣኪ ፡ ሣኪ ፡
« ማንሣ —ማንሣኒያ ፡ ሩም ፡ ሩም ፡ ዊስኪ ፡ ዊስኪ»

ጠጣ ፡ አልነው ፡ ብርሃኗን ፡
ንትርኩ ፡ ይብቃ ፤
ገፍተንልሃል ፡ ሙሉዋን ፡ ጨረቃ !
አታያትም ፡ እንዴ ፡ እሷ ፡ እንኳን ፡ ስትቀብጥ ፡
ጥርስ ፡ ወርቋ ፡ ቦምቤይ ፡ ባሕሩን ፡ ስትገምጥ ?



## ጉድባይ ዳግማዊ *

ጉድባይ ፡ ደህና ፡ ሁኑ ።
አድማችሁ ፡ አይገርምም ፡ አንድነታችሁ ፡
እንደዚህ ፡ ባንደግዜ ፡ የመክዳታችሁ ።
ጥንቱንስ ፡ አንድነት ፡ መች ፡ ተለያችሁ ?
—ካንድ ፡ የፍቅር ፡ ዋንጫ ፡ ስለጠጣችሁ ።

ዋንጫው ፡ ያሳዝናል ፡ ጽዋ ፤ የከበረ ፤
በሕንድ ፡ ሐሩር ፡ ጸሐይ ፡ ክው ፡ እንዳለ ፡ ቀረ ?
ላፍሰው ፡ እንግዲህ ፡ የፍቅርን ፡ ጭላጭ ፡
ካልተገኘች ፡ በቀር ፡ የምትጐነጭ ፡
የናንተን ፡ ትራፊ ፡ የበሰለ ፡ ጠጅ ፡
ሊፕስቲክ ፡ ያልነካት ፡ ያልተማረች ፡ ልጅ ።

ትምጣና ፡ ትቅመሰው ፡ ያን ፡ ጠጅ ፡ ማር —ወለላ ፡
ያን ፡ የቅኔ ፡ መጠጥ ፡ ያን ፡ የጐንደር ፡ ጠላ ፤
—ራሷ ፡ ላይ ፡ ሲወጣ ፡ ትንም ፡ አይላት ፤
ገፈቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተነሣለት ፤
ጉሽነቱም ፡ ቀርቷል ፡ ጠሏል ፡ በመርጋቱ ፤
አሥር ፡ እጅ ፡ ያመጣል ፡ ቃናውም ፡ ከጥንቱ ።

ቤተስኪያን ፡ ስትስሙ ፡ በማቲ ፡ ጫጩት ፡
ቃጅባችሁ ፡ ድንገት ፡ ስንለው ፡ ግጭት ፤
«ጤና ፡ ይስጥልኝ » መቼም ፡ መባባል ፡ አይቀር ፤
ብርሌ ፡ አንገት ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ቢያቀረቅር ፤
እናቲቱ ፡ ዶሮ ፡ ኩፍ —ቁፍፍ ፡ ብትል ፤

ካለፍኩኝ ፡ በኋላ ፡ ሙጫው ፡ ይጠይቃል ፡—
« ያ ፡ ሰውዬ ፡ ማነው ? አጐቴን ፡ ይመስላል ! »
ሲባል ፡ ይታየኛል ፡—«ሌባ ፡ ነው ፡ ሞላጫ»
ለጠያቂው ፡ ኩርኩም ፡ ሲደርሰው ፡ መቀጫ ።

እንጣጣውና ፡ አስታውሰውና ፡
ያጮልሽኝን ፡ ጥፊ ፡ የሸቶሽን ፡ ቃና ፤
በጥሙ ፡ እንዳይገድለኝ ፡ የሜርፔንታይን ፡ ውሀ ፡
ራጃስታን ፡ በረሃን ፡ ልቤ ፡ እንዳይሆን ፡ ስል ፤
ፒጃማ ፡ ለብሼ ፡ አጥሩን ፡ ስዘል ፡
ይታየኛል ፡ ሌሊት ፡ ሲጮሁ ፡ ውሾቹ ።
የኔን ፡ አክሮባቲክ ፡ አያውቁት ፡ ባሎቹ !

ይብላኝ ፡ ለናቶ ፡ ባል ፡ ለሚታለሉት .....
ለባል ፡ ነው ፡ ለሰይጣን ፡ ደሞ ፡ እማዝንለት ?
ማነው ፡ ለነገሩ ፡ የደፈረኝ ፡ ዳንዴ !
መሞቻውን ፡ ይምረጥ ፡ —ሽጉጥ ፡ ነው ፡ ጐራዴ ?
መጣሁልህ ፡ በይው ፡ መግቢያህን ፡ ፈልግ ፡
እኔ ፡ አንተን ፡ ብገድል ፡ አልወጣም ፡ ከሕግ ።
ኑዛዜውን ፡ ይንገር ፡ ለንስሐ ፡ አባቱ ፡
ወንድ ፡ እንደሆን ፡ ይሙት ፡ ለሴት ፡ ለመሬቱ !

ተሸነፍኩ ፡ እባክሽ ፡ ተረታሁኝ ፡ እኔ ፡
እጄን ፡ ልስጥ ፡ እንግዴህ ፤ ነውና ፡ ተገቢ ፤
ድል ፡ የነሣቻችሁ ፡ ትማርከኝ ፡ ፑንጃቢ ።
ጉድባይ ፤ ደህና ፡ ሁኑ ።



# ጉባኤ ቃና *

ሰማይ ፡ ጠቀስ ፡ ሆነ ፤ ሚሱሪ ፤ ኩራቴ ፡
በላዩን ፡ ደመናን ፡ የዝቅዝቅ ፡ ማየቴ ፤
ሰማይ ፡ ጠቀስ ፡ ሆነ ፤ ሚሱሪ ፤ ኩራቴ ።

# ማስታወሻ

ለአንባቢዎች ፡ ምናልባት ፡ ዕንግዳ ፡ የሚሆን ፡ አን ዳንድ ፡ ነገር ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ማጋጠሙ ፡ ስለማይቀር ፤ ለማብራሪያ ፡ ያህል ፡ የሚለጥቁትን ፡ ማሳሰቢያዎች ፡ በየ ግጥሙ ፡ አርዕስት ፡ ለይተን ፡ አመልክተን ፡ አቅርበናል።

## ሕይወት

ሀ/ «ኩሉ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ አምጣነ ፡ ልቡና ፡ ኢይመውት»

—ከሀገራችን ፡ ቅኔ ።

ለ/ ዝም ፡ የቁጥር ፡ መጨረሻ ነው ፡— በእንግሊዝኛ ፡ «ኢንፊኒቲ» ፡ እንደሚባለው ፡ ያለ ።

## ትዝታ

ሀ/ የሎንዶን ፡ ጭጋግ ፡ የታወቀ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ነው ።

ለ/ በደቡብ ፡ ኢንግላንድ ፡ ገበሬዎች ፡ የሚከምሩት ፡ የሣር ፡ ድርቆሽ ፡ ክሩቅ ፡ ሲያዩት ፡ ልክ ፡ ያገራችንን ፡ የሣር ፡ ቤት ፡ ይመስላል ።

## አገሩ ፡ ገቢ

ሀ/ አውሮፕላን ፡ በጋኔን ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ የሚሔድ ፡ ብለው ፡ የሚያምኑና ፤ ዓለምን ፡ ዙሪያዋን ፡ ሆነው ፡ የያዝዋት ፡ ሁለት ፡ ዘንዶዎች ፡ መኖራቸውን ፡ የሚያ ምኑ ፡ ሰዎች ፡ በሀገራችን ፡ ሞልተዋል ።

ለ/ ከማል ፡ አታቱርክ ፡ የሀገሩን ፡ የቱርክን ፡ ሕዝብ ፡ ለማሠልጠን ፡ ሲል ፤ ጠርቡሻቸውን ፡ አውልቀው ፡ ባር



ኔጣ ፡ እንዲያጠልቁ ፤ ጢማቸውን ፡ እንዲላጩ ፡ በአ ዋጅ ፡ አስገድዷቸዋል ። ይህ ፡ የሆነው ፡ ከመጀመሪ ያው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ነው።በኛ ፡ አገር ፡ ግን ፡ እስካሁን ፡ ያልሰሙት ፡ አሉ ።

## ውኃ ፡ ,ማያጠፋው

ሀ/ «ማይ ፡ ብዙህ ፡ ኢይክል ፡ አጥፍኦታ ፡ ለፍቅር » ይላል ፡ ሰሎሞን ፡ በመሐልየ ፡ መሐልዩ ።

## ጉድባይ

ሀ/ «ፍቅር ፡ ያልቅና ፡ ሲሆን ፡ ግትቻ ፡
ንዝንዝና ፡ ጭቅጭቅ ፡ ብቻ»
—የሚል ፡ ያገራችን ፡ ዘፈን ፡ አለ ።

## ኪስ

ሀ/ « ኪስ » በእንግሊዝኛና ፡ በአማርኛ ፡ ድምጹ፡አንድ ፡ ዓይነት ፡ ቢሆንም ፡ ፍቺው ፡ እየቅል ፡ ነው ። ይህች ፡ የጨዋታ ፡ ግጥም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተች ፡ ናት።

## የወንድ ፡ ልጅ ፡ ያለህ

ሀ/ እርትሳ — ኪት ፡ የታወቀች ፡ ጥቁር ፡ አሜሪካን ፡ ድምፃዊ ፡ ተጨዋች ፡ አርቲስት ፡ ናት ። እዚህ ፡ የጠቀ ስኩት ፡ «ሊትስ— ዱ— ኢት» የሚለውን ፡ አስደሳች፡ ዘፈኑዋን ፡ ነው ።

ለ/ «ሮማንስ » በየሲኒማው ፡ የሚታየው ፡ ዓይነት ፡ ዘመ ናይ ፡ ፍቅር ፡ ነው ።

## በገላጋይ ፤

ሀ/ «እናትና ፡ አባትሽ ፡ በፍቅር ፡ አረጁ ፡
ምነው ፡ ለኛ ፡ጊዜ ፡ ሠንሠለት ፡ አበጁ ? »
— የሚል ፡ ያገራችን ፡ ግጥም ፡ አለ ።

## እናትና ፡ ልጅ

ሀ/ አስትሮኖሚ ፡ የኰከብ ፡ ቈጠራ ፡ ሳይንስ ፡ ነው ።
ጥንቈላ ፡ ሳይንስ ፡ አይደለም ።

ለ/ «ሴንትሪፉጋል — ፎርስ » ማንኛውንም ፡ የሚዞር ፡ ወይም ፡ የሚሽከረከር ፡ ነገር ፡ ከመሥመሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የሚገፈትረው ፡ ኃይል ፡ ነው።

ሐ/ ጨረቃን ፡ የመረመሩ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ውኃ፡ ቅጠል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ የሕይወት ፡ ምልክት፡ የለባትም ፡ ይላሉ ።

## ሕንደኬ

ሀ/ ዝርባን፡ በላብ፡ የሚያስለቅስ፡ የሕንድ፡ አገር ፡ ዋዕይ፡ ነው ።

ለ/ ካልካታ ፡ ብዙ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ የሚኖርበት ፡ ከተማ ፡ ነው ።

ሐ/ቪኖባ—በሃቬ፡ በስተርጅና፡ በእግሩ፡ ከወረዳ፡ ወደወረዳ፡ እየሄደ ፡ መሬት ፡ ካላቸው ፡ ባለጸጎች ፡ እየለመነ ፡ ለሌ



ላቸው ፡ ድሆች ፡ የሚያካፍል ፡ ጻድቅ ፡ የጋንዲ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ሐዋርያ ፡ ነው ።

## ማ ና ሊ

ሀ/ ማናሊ ፡ በረዶ ፡ በተጐናጸፈው ፡ በሂማላያ ፡ ተራራ ፡ ግርጌ ፡ የምትገኝ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ትንሽ ፡ ከተማ፡ ነች ።

## ቦምቤይ

ሀ/ በቦምቤ፡ ወደብ፡ ከተማ፡ አልኮላዊ፡ መጠጥ፡ በፍጹም፡ በሕግ ፡ ተከልክሏል ።

ለ/ ሣኪ ፡ —የጃፓን ፡ መጠጥ ፡
ማንሣኒያ ፡ —የእስፓኝ ፡ መጠጥ ፡
ሩም ፡ —የኩባ ፡ ጠጅ

## ጉድባይ ፡ ዳግማዊ

ሀ/ ሤርፔንታይን ፡ የሎንዶን ፡ ፍቅረኞች፡ በጀልባ ፡ ሽር፡ ሽር ፡ የሚሉበት ፡ ነው ።

ለ/የራጃስታን ፡ በረሃ ፡ ለኒው ፡ ዴልሂ ፡ ቅርብ ፡ ነው ።

## ጉባኤ ፡ ቃና

ሀ/ሚሱሪም ፡ እንደ ፡ ማናሊ ፡ ያለች ፡ ከተማ ፡ ናት ።
በከፍተኛ ፡ ጋራ ፡ ቁንጮ ፡ ቁብ ፡ ብላለች ።

---

ለመተርጐም ፡ ለማሳተም ፡ ወይም፡ ለማራባት ፡ የደራሲው ፡ ፈቃድ፡ ያስፈልጋል ።



SCHOOL OF ORIENTAL & AFRICAN STUDIES